# ትንቢተ ሆሴዕ

## መግቢያ

### ጸሐፊውና የተጻፈበት ጊዜ

የብኤሪ ልጅ ሆሴዕ ይህን የትንቢት ቃል የተናገረው፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በስምንተኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ገደማ ሲሆን፣ አገልግሎቱን የጀመረው አሞጽ በነበረበት ወቅት ወይም ከእርሱም በኋላ ወዲያውኑ ሊሆን ይችላል:: አሞጽ ማንነቱ ባልታወቀ ጠላት አማካይነት በእስራኤል ላይ ስለሚመጣው የእግዚአብሔርን ፍርድ ይናገራል፤ ሆሴዕ ግን ይህ ጠላት አሦር እንደ ሆነ ይገልጻል (7፥11፤ 8፥9፤ 10፥6፤ 11፥11):: ከመጽሐፉ ውጪ ስለ እርሱ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፣ በ1፥1 ላይ የተጠቀሱትን ነገሥታት ስንመለከት ሆሴዕ ቢያንስ ለሠላሳ ስምንት ዓመት ያህል ትንቢት መናገሩን እንገነዘባለን:: እርሱም ከሰሜኑ መንግሥት (ከእስራኤል) በመምጣት፣ የትንቢት ቃል ከጻፉት ነቢያት መካከል ብቸኛ ነቢይ ነበር፤ የተናገረውም ትንቢት በመጀመሪያ የመጣበትን መንግሥት የሚመለከት ነው:: ነቢያዊ አገልግሎቱ የሚታወቀው ከይሁዳ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት ጋር በማገናዘብ ስለ ሆነ፣ ምናልባት መጽሐፉ የተጻፈው የሰሜኑ መንግሥት ዋና ከተማ የነበረችው ሰማርያ ከወደቀች በኋላ በይሁዳ ሊሆን ይችላል:: ይሁዳ በመጽሐፉ ውስጥ መጠቀሱም ይህንን ግምት ያጠናክርልናል (1፥7:11፤4፥15፤5፥5:10:13፤6፥4:11፤10፥11፤11፥12፤12፥2):: ይህን መጽሐፍ የጻፈው ሆሴዕ ይሁን ወይም ሌላ ሰው በውል የሚታወቅ ነገር የለም:: የሆሴዕ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ አከፋፈል መሠረት በታናናሽ ነቢያት ወይም የትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ቀዳሚ ሆኖ የሚገኝ ነው፤ 'ታናናሽ የትንቢት መጻሕፍት የሚለው ስያሜ" ከኢሳይያስ፣ ከኤርምያስና ከሕዝቅኤል የትንቢት መጻሕፍት ጋር ሲነጻጸሩ አጫጭር መሆናቸውን የሚገልጽ ነው::

### ታሪካዊ ዳራው

ሆሴዕ የኖረው የሰሜኑ መንግሥት እጅግ አሳዛኝ ደረጃ ላይ ደርሶ በነበረበት በመጨረሻው ጊዜ ላይ ሲሆን፣ ይኸውም ከዳግማዊ ኢዮርብዓም ቀጥሎ በሃያ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ (2ነገ15፥8-17፥41) ስድስት ነገሥታት በሚገዙበት ወቅት ነበር:: ከእነዚህም ውስጥ ዘካርያ፣ ሰሎም፣ ፋቂያስና ፋቁሔ የተባሉት አራቱ በሥራ ገበታቸው ላይ እንዳሉ ሥልጣናቸውን ቀምተው በያዙ ሰዎች ተገድለዋል፤ ሆሺዕ በጦርነት ተሸንፎ ወደ ግዞት የወረደ ሲሆን፣ መንግሥቱን ለልጁ ያወረሰው ምናሔም ብቻ ነው:: እግዚአብሔር እነዚህን ነገሥታት ለእስራኤል ሲሰጥ በቍጣ ነበር፤ የተሻሩትም በመዓቱ ነው (13፥11)፤ እርሱም በውሃ ላይ እንዳለ ኩበት አደረጋቸው (10፥7)፤ ያለማቋረጥ የደም መፋሰስ ሆነ (4፥2):: አሦር ወደ ምዕራብ እየገፋ ሲመጣ፣ ምናሔም ይህንን በዓለም የገነነ መንግሥት የበላይ ገዥ አድርጎ በመቀበል ግብር ገበረለት (2ነገ 15፥19-20):: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በ733 ዓ.ቅ.ክ. ፋቁሔ በሠራው ተንኰል ምክንያት አሦር ከእስራኤል ላይ ብዙዎቹን ግዛቶች ከፍሎ ወሰደ፤ ለእስራኤልም ንጉሥ የቀረው የኤፍሬም ግዛቶችና ከምናሴ ግዛት ምዕራቡ ክፍል ብቻ ነበር:: ከፋቁሔም ቀጥሎ የነገሠው አውሴን ሲሆን፣ እርሱም (ለአሦር ንጉሥ) ታማኝ ሆኖ ስላልተገኘ፣ ሰማርያ ተያዘች፤ ሕዝቧም በምርኮ ተጋዘ (722-721 ዓ.ቅ.ክ)፤ በዚህም ምክንያት የሰሜኑ መንግሥት ወደቀ::

### መሪ ሐሳቡና መልእክቱ

ከምዕራፍ 1-3 ያለው የመጽሐፉ የመጀመሪያ ክፍል፣ ነቢዩ ከእግዚአብሔር ለሕዝቡ የተቀበለውን መልእክት ለማስተላለፍ የሆሴዕን የቤተ ሰብ ሁኔታ እንደ ምሳሌ ወስዶ ይተርካል:: እግዚአብሔር ሆሴዕን ጋለሞታዪቱን ጎሜርን እንዲያገባ አዘዘው:: ሦስቱም ልጆቻቸው እያንዳንዳቸው ሊመጣ ያለውን ክፉ ነገር (ፍርድ) በማሳየት እንደ ተምሳሌት የሚያገለግሉ ስሞች ሰጣቸው:: ምዕራፍ ሁለት፣ ሆሴዕ ከጎሜር ጋር የነበረውን ግንኙነት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ካለው ግንኙነት ጋር ያነጻጽራል፤ ልጆቹ ታማኝ ያልሆነችውን እናታቸውን ከቤታቸው እንዲያባርሩ ተነግሯቸዋል:: ይሁን እንጂ ይህ የሆነው ባለመፈለጓ (ነጻ እንድትወጣ) ሳይሆን ተሐድሶ እንድታገኝ ነበር:: ነቢዩም ካገባት በኋላ ከእርሱ ተለይታ ሄዳ ብታመነዝርም፣ አሁንም እንዲያፈቅራት ይታዘዛል፤ እርሱም እርሷን መልሶ በማምጣት ለተወሰነ ጊዜ ለብቻዋ እንድትሆን አደረጋት (ም 3):: ይህም የብልጽግናቸው ምንጭ አድርጋ በመቍጠር የከነዓናውያንን አማልክት በማምለክ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ ካልሆነችው እስራኤል ጋር እግዚአብሔር የነበረውን ግንኙነት ሥዕላዊ በሆነ መንገድ የሚያሳይ ነው (ከ2፥4:9 እና 18 ጋር ያነጻጽሩ):: እስራኤል ለተወሰነ ዘመን በስደት ኖረች (ከ7፥16፤ 8፥14፤ 9፥3:6:17፤ 11፥5 ጋር ያነጻጽሩ):: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳን ሕዝቡ የነበረው ፍቅር አልተቋረጠም፤ ሆሴዕ ጎሜርን መልሶ እንደወሰዳት፣ ሁሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደራሱ ሊመልስ ወደደ:: ይህም እስራኤላውያን ከግብፅ ወጥተው በከነዓን ምድር መስፈራቸውን በሚያስታውስ መልኩ በዘይቤያዊ አነጋገር ተገልጾአል (ከ1፥11፤ 2፥14-23፤ 3፥5፤ 11፥10-11፤ 14፥4-7 ጋር ያነጻጽሩ):: እስራኤል ቀድሞ ከእግዚአብሔር ጋር ያሳለፈችው ሁኔታ ወደ ፊት ከሕዝቡ ጋር ላለው ግንኙነት መሠረታዊ ሞዴል ወይም ምሳሌ እንደ ሆነ ሆሴዕ ተገንዝቦአል::

ከምዕራፍ 4-14 ያለው ሁለተኛው የመጽሐፉ ክፍል፣ እስራኤል በከነዓናውያን እምነት መጠመዷን በዝርዝር ይገልጻል፤ ሆኖም የዚህን ክፍል አስተዋፅኦ ሥርዐት ባለው መንገድ ማስቀመጥ አስቸጋሪ

ነው:: እንደ ሌሎቹ የትንቢት መጻሕፍት ሁሉ፣ ትንቢተ ሆሴዕም ለንስሓ ጥሪ ያደርጋል:: እስራኤልም ያላት አማራጭ ጣዖቷን በመጣል ወደ እግዚአብሔር መመለስ ብቻ ነው (ም 6፤ 14)::

የእስራኤላውያን ትልቁ ችግር እግዚአብሔርን አለማወቃቸው እንደ ሆነ ሆሴዕ ተገንዝቦአል:: (4፥6፤ 13፥4):: እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የነበራት ግንኙነት የፍቅር ነበር (2፥19፤ 4፥1፤ 6፥6፤ 10፥12፤ 12፥6)፤ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለው ቃል ኪዳናዊ ወዳጅነት፣ በመጀመሪያው የመጽሐፉ ክፍል የተገለጸው በባልና በሚስት መካከል ባለው ግንኙነት ሲሆን፣ በኋላም በአባትና በልጅ መካከል ባለው ግንኙነት ጉላ ብሎ ተገልጾአል (11፥1-4):: ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆን መንፈሳዊ ግልሙትና ነው (4፥13-14፤ 5፥4፤ 9፥1 ይመ፤ ከኤር 3 ጋር ያነጻጽሩ):: እስራኤል በቤተ ጣዖት ምን ዝርናን በመፈጸም (4፥14)፣ ወደ በአል አምልኮ በመመለስ፣ አሕዛብ በሚያመልኩባቸው ኰረብቶች ላይ መሥዋዕት አቀረበች፤ በሰማርያ ለጥጃ ምስል ሰገደች (8፥5፤ 10፥5-6፤ 13፥2):: እነርሱንም መሸሸጊያ መከታ በማድረግ በእነርሱ ሐሳብ ነጐደች (5፥13፤ 7፥8-11):: ከዚህ የተነሣ ከእግዚአብሔር የከፋ ፍርድ እንደሚጠብቃት የተገለጸ ቢሆንም፣ የመጽሐፉ ዋና ሐሳብ ግን የእግዚአብሔር ርኅራኄና ፍቅር እስራኤልን አውጥቶ የማይጥል መሆኑን የሚያሳይ ነው::

## ልዩ ትኩረት የሚጠይቁ ጉዳዮች

የሆሴዕ መጽሐፍ ሁለት ጥንቃቄ የሚሹ ችግሮች አሉት:: የመጀመሪያው ከም 1-3 ያለው ታሪክ ይዘትና የጎሜር ባሕርይ ነው:: አንዳንድ ምሁራን "ይህ ታሪክ በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለውን ግንኙነት ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ የሚያሳይ ብቻ ነው" ሲሉ ሌሎች ደግሞ ጠንካራ ማስረጃዎችን በማቅረብ ታሪኩ መተርጐም ያለበት ቃል በቃል እንደሆነ ይናገራሉ:: የሁለተኛው ዐይነት አመለካከት ካላቸው ምሁራን መካከል "ጎሜር አስቀድሞ ታማኝ ነበረች፤ ኋላ ግን ታማኝነቷን ጥላለች" ሲሉ ሌሎች ደግሞ፣ "ከጋብቻም በፊት እንኳን ቢሆን ታማኝ አልነበረችም" በማለት ይናገራሉ::

ሁለተኛው ችግር ም 3 ከም 1 ጋር ያለው ግንኙነት ነው:: በም 3 ውስጥ ስለ ልጆቹ የሚገልጽ ነገር ባይኖርም አንዳንድ ምሁራን ሁለቱ ምዕራፎች በአንድ ወቅት ውስጥ የተከናወኑ ሁለት የተለያዩ ታሪክ ነው በማለት ይናገራሉ:: ሆኖም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው አተረጓጐም ትክክል እንደ ሆነ ይታመናል:: ይኸውም ም 3 ከም 1 የሚለጥቅ ተከታታይ ታሪክ ነው፤ ጎሜር ታማኝ አለመሆኗ ከተረጋገጠ በኋላም ሆሴዕ መልሶ እንዲወስዳት ታዞአል የሚል ነው::

## አስተዋፅኦ

1. መግቢያ (1፥1)
2. ጋለሞታዪቱ ሚስትና ታማኙ ባል (1፥2-3፥5)
   - ሀ. የልጆቹ ምልክት መሆን (1፥2-2፥1)
   - ለ. ጋለሞታዪቱ ሚስት (2፥2-23)
     1. የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ (2፥2-13)
     2. እግዚአብሔር እስራኤልን እንደ ገና እንደሚሠራት (2፥14-23)
   - ሐ. ታማኙ ባል (ም 3)
3. ልቡ ከእግዚአብሔር የራቀ ሕዝብና ታማኙ አምላክ (ም 4-14)
   - ሀ. እስራኤል ታማኝ ሆና አለመገኘቷ (4፥1-6፥3)
     1. የቀረበው ክስ (4፥1-3)
     2. የክሱ ምክንያትና የሚከተለው ውጤት (4፥4-19)
     3. ሕዝቡንና መሪዎችን የሚመለከት ልዩ መልእክት (ም 5)
     4. አሳዛኝ ልመና (6፥1-3)
   - ለ. የእስራኤል መቀጣት (6፥4-10፥15)
     1. የፈጸሙት በደል መገለጹ (6፥4-7፥16)
     2. ፍርድ መታወጅ (ም 8-9)
     3. እጣሪና አቤቱታ (ም 7-10)
   - ሐ. የእግዚአብሔር ፍቅር (ም 11-14)
     1. የእግዚአብሔር አባታዊ ፍቅር (11፥1-11)
     2. ታማኝ ባለ መሆኗ የእስራኤል መቀጣት (11፥12-13፥16)
     3. ከንስሓ በኋላ የእስራኤል ተሐድሶ (ም 14)

1 በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያን፣ በኢዮአ
ታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን እን
ዲሁም በእስራኤል ንጉሥ በዮአስ[ሀ] ልጅ
በኢዮርብዓም ዘመን ወደ ብኤሪ ልጅ ወደ
ሆሴዕ የመጣው *የእግዚአብሔር* ቃል ይህ
ነው፤

## የሆሴዕ ሚስትና ልጆቹ

2 *እግዚአብሔር* በሆሴዕ መናገር በጀመረ
ጊዜ፣ *እግዚአብሔር* "ምድሪቱ *ከእግዚአ
ብሔር* ተለይታ ታላቅ ምንዝርና እያደረ
ገች ስለ ሆነ፣ ሄደህ አመንዝራ ሴት
አግባ፤ የምንዝርና ልጆችንም ለራስህ ውሰድ"
አለው። 3 ስለዚህ እርሱ የዴቤላይምን ሴት
ልጅ ጎሜርን አገባ፤ እርሷም ፀነሰች፤ ወንድ
ልጅም ወለደችለት።

4 *እግዚአብሔርም* ሆሴዕን እንዲህ አለው፤
"በኢይዝራኤል ስለ ተፈጸመው ግድያ የኢ
ዩን ቤት በቅርቡ ስለምቀጣና የእስራኤል
ንም መንግሥት እንዲያከትም ስለማደርግ፣
ስሙን ኢይዝራኤል ብለህ ጥራው። 5 በዚ
ያም ቀን በኢይዝራኤል ሸለቆ፣ የእስራኤ
ልን ቀስት እሰብራለሁ።"

6 ጎሜር እንደ ገና ፀነሰች፤ ሴት ልጅም
ወለደች፤ *እግዚአብሔርም* ሆሴዕን እንዲህ
አለው፤ "ይቅር እላቸው ዘንድ ለእስራኤል
ቤት ከእንግዲህ ስለማልራራላቸው፣ ስሟን
ሎሩሃማ[ለ] ብለህ ጥራት። 7 ነገር ግን ለይሁዳ
ቤት እራራለሁ፤ በቀስት ወይም በሰይፍ
ወይም በጦርነት ወይም በፈረሶችና በፈረሰ
ኞች ሳይሆን በአምላካቸው *በእግዚአብሔር*
አድናቸዋለሁ።"

8 ጎሜር፣ ሎሩሃማን ጡት ካስጣለች በኋላ
ሌላ ወንድ ልጅ ወለደች። 9 *እግዚአብሔ
ርም* እንዲህ አለው፤ "ሎዓሚ[ሐ] ብለህ ጥራው፤
ምክንያቱም እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም፤
እኔም አምላካችሁ አይደለሁምና።

10 "ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ሊሰፈርና
ሊቈጠር እንደማይችል እንደ ባሕር አሸዋ
ይሆናሉ፤ 'ሕዝቤ አይደላችሁም' በተባሉ
በት ቦታ፣ 'የሕያው አምላክ ልጆች' ተብ
ለው ይጠራሉ። 11 የይሁዳ ሕዝብና የእስራ
ኤል ሕዝብ እንደ ገና አንድ ይሆናሉ
አንድ መሪም ይሾማሉ፤ አንድ ሆነውም
በምድሪቱ ይገናሉ፤ የኢይዝራኤል ቀን ታላቅ
ይሆናልና።

2 "ወንድሞቻችሁን 'ሕዝቤ'፣ እኅቶቻች
ሁንም 'ተወዳጆቼ' ብላችሁ ጥሯቸው።

## የእስራኤል መቀጣትና መመለስ

2 "እናታችሁን ምከሯት፤ ምከሯት፤
እርሷ ሚስቴ አይደለችም፤
እኔም ባሏ አይደለሁምና።
ከፊቷ የዘማዊነት አስተያየትን፣
ከጡቶቿም መካከል ምንዝርናዋን
ታስወግድ።
3 አለበለዚያ ገፍፌ ዕርቃኗን
አስቀራታለሁ፤
እንደ ተወለደችበትም ቀን
አደርጋታለሁ፤
እንደ ምድረ በዳ፣

[ሀ]1 በዕብራይስጥ ዮአስ የሚለው ቃል የኢዮአስ አማራጭ ትር
ጕም ነው [ለ]6 ሎሩሃማ ማለት ያልተወደደች ማለት ነው
[ሐ]9 ሎዓሚ ማለት ሕዝቤ አይደለም ማለት ነው

1፥1 2ነገ13፥13፤ 14፥21፤1ዜና3፥12፡13፤ኢሳ1፥1፤ኤር1፥2፤ሚክ1፥1፤አሞ1፥1
1፥2 ዘዳ31፥16፤ኤር3፥1፡14፤ሕዝ 23፥3-21፤ ሆሴ2፥2፡5፤3፥1፤5፥3
1፥3 ቍ6
1፥4 ቍ11፤1ሳሙ29፥1፤1ነገ18፥45፤2ነገ10፥1-14፤ሆሴ2፥22
1፥5 ኢሱ15፥56፤1ሳሙ29፥1፤2ነገ15፥29
1፥6 ቍ3፡8፤ሆሴ2፥4፡23
1፥7 መዝ44፥6፤ዘካ4፥6
1፥8 ቍ6
1፥9 ቍ10፤ሕዝ11፥19-20፤1ጴጥ2፥10
1፥10 ቍ9፤ዘፍ22፥17፤ኢሱ3፥10፤ኤር33፥22፤ሆሴ2፥23፤ሮሜ9፥26
1፥11 ቍ4፤ኢሳ11፥12፡13፤ኤር23፥5-8፤30፥9፤ሕዝ37፥15-28
2፥1 ቍ23፤1ጴጥ2፥10
2፥2 ቍ5፤ኢሳ1፥21፤50፥1፤ሕዝ23፥45፤ሆሴ1፥2፤4፥5
2፥3 ኢሳ32፥13-14፤ሕዝ16፥4፡22፡37

1፥1 *ዖዝያን፤* ከ792-740 ዓ.ቅ.ክ. የነገሠ ሲሆን *ኢዮአታም፤* ከ750-532፤ *አካዝ፤* ከ735-715፤ *ሕዝቅያስ፤* ከ729-686 ዓ.ቅ.ክ. በይሁዳ ላይ ነግሠዋል። ከላይ ከተጠቀሱት የአገዛዝ ዘመናት የአንዳንዶቹ ተደራርበዋል፤ ከእነዚህም መካከል የአካዝና የሕዝቅያስ አብሮ የመግዛት ዘመን ከሁሉ ይልቅ ረጅም ነበር (ኢሳ 36፥1 ማብ ይመ)። *ኢዮርብዓም፤* ከ793-753 ዓ.ቅ.ክ. የነገሠው ዳግማዊ ኢዮርብዓም ነው። ሆሴዕ፣ በኢሳይያስ፣ በአሞጽና በሚክያስ ዘመን የኖረ ነቢይ ነው፤ በየመጽሐፎቻቸው 1፥1 ላይ ይመ። *ሆሴዕ፤* "ድነት" ማለት ነው። *የእግዚአብሔር ቃል፤* በኢዩኤል (1፥1)፣ በሚክያስና (1፥1) በዘካርያስ (1፥1፡7) ከተጠቀሰው ጋር የሚመሳሰልና ሥልጣንን የሚያመለክት ነው።

1፥2 *አመንዝራ ሴት አግባ፤* በመግቢያው ላይ፣ "ለየት ያሉ ችግሮች" የሚለውን ይመ። *የምንዝርና፤* እግዚአብሔር እስራኤልን የሚወቅስበት ዋነኛ ኀጢአት ነው።

1፥3 *ጎሜርም፤* ከዚህ መጽሐፍ ውጭ በሌላ ስፍራ አልተጠቀሰችም።

1፥4 *በኢይዝራኤል፤* የቃሉ ትርጕም እግዚአብሔር ይበትናል ማለት ሲሆን፣ በዚህ ስፍራ በገዦች ላይ ይፈጸም ዘንድ የተነገረውን ፍርድ የሚያጸና ነው (የቍ 11፤2፥22 ማብ ይመ)። ዳግማዊ ኢዮርብዓም፣ የአክአብን ልጅ የኢዮራምን መንግሥት በመገልበጥ (2ነገ 9፥14-37 ይመ፤ ከ1ነገ19፥16-17 ጋር ያነጻጽሩ) በኢይዝራኤል ከተመሠረተው ከኢዩ ሥርወ መንግሥት የመጣ ነው (በ841-814 ዓ.ቅ.ክ)፤ የኢዩ ሥርወ መንግሥት ያከተመው ዘካርያስ በተገደለበት በ753 ዓ.ቅ.ክ. ነው (2ነገ 15፥8-10)።

1፥5 *የእስራኤልን ቀስት፣* ምንም እንኳ ሰማርያ ለሁለት ዓመት ያህል በጠላት ተከባ ብትቈይም (2ነገ 17፥5-6)፣ የእስራኤል መከላከያ ኀይል የተንኰታኰተው በ724 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ ነው።

1፥6 *ሎሩሃማ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ይህ ስም እግዚአብሔር ቀድሞ ለእስራኤል የነበረው ፍቅር መለወጡን የሚያመለክት ነው (ዘፀ 33፥19፤ ዘዳ 7፥6-8)፤ በኋላ ግን ይህ ፍቅር እንደሚታደስ ተስፋ ተሰጥቶአል (2፥23)።

1፥7 *ለይሁዳ... አድናቸዋለሁ፤* ከ722-721 ዓ.ቅ.ክ. እንዲሁም በ701 ዓ.ቅ.ክ. (2ነገ 19፥32-36 ይመ) እግዚአብሔር ይሁዳን ከአሦር እጅ ታድጎአል።

1፥9 *ሎዓሚ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ይህ ስም በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል ያለው የቃል ኪዳን ግንኙነት መቋረጡን (ዘፀ 6፥7፤ ኤር 7፥23 ይመ) የሚያመለክት ሲሆን፣ ወደ ፊት ግን ይታደሳል (ቍ 10፤ 2፥1፡23)። ማስጠንቀቂያው ከመጀመሪያው ልጅ ወደ ሦስተኛው ልጅ እየጠነከረ ሄዶአል።

*1፥10፤* በሮሜ 9፥26፤ 1ጴጥ 2፥10 ላይ የተጠቀሰ ሲሆን፣ አሕዛብን ከሚመለከት የወንጌል ተልእኮ ጋር የተያያዘ ነው። *ይሁን እንጂ፤* ለተወሰነ ጊዜ አስፈሪ ቅጣት እንደሚኖርና (ቍ 4-9) በኋላም የበረከት ጊዜ እንደሚመጣ ያሳያል። *እንደ ባሕር አሸዋ፤* ለአብርሃምና ለያዕቆብ የተሰጠውን ተስፋ በዘፍ 22፥17፤32፥12 ላይ ይመ፤ ከኤር 33፥22፤ ዕብ 11፥12 ጋር ያነጻጽሩ። *ልጆች፤* በ2፥2፡4 ላይ የምንዝርና ልጆች ተብሎ ከተጠቀሰው ጋር የሚነጻጸር ነው (ዘዳ 32፥17)።

1፥11 *እንደ ገና አንድ ይሆናሉ፤* እስራኤልና ይሁዳ ተመልሰው አንድ ሕዝብ እንደሚሆኑ ያመለክታል። ወይም እንደ ተክል ከምድር ብቅ ይላሉ ማለት ሊሆን ይችላል። *በምድሪቱ፤* በምርኮ የነበሩበት አገር ሳይሆን አይቀርም (ከዘፀ 1፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። *ኢይዝራኤል፣* የቍ 4 ማብ ይመ። እዚህ ላይ ግን "እግዚአብሔር ይበትናል" የሚለው ዐረፍተ ነገር መዝራትን ወይም መትከልን ያመለክታል፤ ይህም የመጀመሪያው ልጅ ስም ትርጕም መለወጡን ያሳያል (2፥21-23) ይመ።

2፥1 *ሕዝቤ... ተወዳጆቼ፤* ከሆሴዕ ልጆች ስም ጋር የተገናኙ መጥፎ ነገሮች አልተጠቀሱም (የ1፥6፡9 አማራጭ ትርጕም ይመ)።

2፥2 *ሚስቴ አይደለችም፤* በዝሙት ምክንያት ጋብቻቸው ፈርሶአል፤ ይሁን እንጂ የተፈለገው ፍች ሳይሆን ዕርቅ ነበር፤ ከቍ 7-15 ጋር ያነጻጽሩ።

2፥3 *ገፍፌ፤* ሚስቱ የምትለብሳቸውን ልብሶች የሰጣት ባሏ ነው (ዘፀ 21፥10፤ ሕዝ 16፥10 ይመ)፤ እዚህ ላይ ግን ታማኝ አለ

እንደ ደረቅም ምድር አደርጋታለሁ፤
በውሃ ጥምም እገድላታለሁ።
4ለልጆቿ አልራራላቸውም፤
የምንዝርና ልጆች ናቸውና።
5እናታቸው አመንዝራ ነች፤
በውርደትም ፀንሳቸዋለች፤
እርሷም፣ ‘እንጀራዬንና ውሃዬን
ይሰጡኛል፤
ሱፌንና የሐር ልብሴን፣ ዘይቴንና
መጠጤን ይሰጡኛል፤
ስለዚህ ውሽሞቼን ተከትዬ እሄዳለሁ’
አለች።
6በዚህ ምክንያት መንገዷን በእሾህ
እዘጋለሁ፤
መውጫ መንገድ እንዳታገኝም ዙሪያዋን
በግንብ አጥራለሁ።
7ውሽሞቿን ተከትላ ትሄዳለች፤ ነገር ግን
አትደርስባቸውም፤
ትፈልጋቸዋለች፤ ሆኖም አታገኛቸውም።
ከዚያም እንዲህ ትላለች፤
‘ወደ ቀድሞ ባሌ እመለሳለሁ፤
የፊተኛው ኑሮዬ ከአሁኑ ይሻለኛልና።’
8እርሷም እህል፣ ዘይትና አዲስ የወይን
ጠጅ የሰጧት፣
ለበኣል አምልኮ ያደረጉትን፣
ብርንና ወርቅን ያበዛሁላት፣
እኔ እንደ ሆንሁ አላወቀችም።
9“ስለዚህ እህሌን በመከር ጊዜ፣
አዲሱም የወይን ጠጅ በደረሰ ጊዜ
እወስዳለሁ፤
ዕርቃኗንም እንዳትሸፍንበት፣
ሱፍና የሐር ልብሴን መልሼ
እወስድባታለሁ።
10አሁንም በውሽሞቿ ፊት፣
ነውሯን እገልጣለሁ፤
ከእጄም የሚያድናት የለም።
11የደስታ በዓሎቿን ሁሉ፣
የዓመት በዓሎቿንና፣ የወር መባቻዎቿን
ሰንበቶቿንና የተመረጡ በዓሎቿን ሁሉ
አስቀራለሁ።
12ከውሽሞቼ የተቀበልሁት ዋጋ ነው
የምትለውን፤
የወይን ተክሎቿንና የበለስ ዛፎቿን
አጠፋለሁ፤
ጫካ አደርገዋለሁ፤
የዱር አራዊትም ይበሉታል።
13ለበኣል አማልክት፣ ዕጣን ስላጠነችባቸው
ቀናት እቀጣታለሁ፤
በጌጣ ጌጥና በቀለበቶች ራሷን አስጊ
ጣለች፤
ውሽሞቿንም ተከትላ ሄዳለች፤
እኔን ግን ረስታለች”
ይላል እግዚአብሔር።
14“ስለዚህ እነሆ፤ አባብላታለሁ፤
ወደ ምድረ በዳም እወስዳታለሁ፤
በፍቅር ቃል አነጋግራታለሁ።
15በዚያም የወይን ተክሏን እመልስላታለሁ፤
የአኮርንም[m] ሸለቆ የተስፋ በር
እንዲሆናት አደርጋለሁ።
በዚያም ከግብፅ እንደ ወጣችበት ቀን፣

2፥4 ሕዝ8፥18፤ ሆሴ1፥6፤5፥7
2፥5 ኤር3፥6፤ 44፥17፤18፤ሆሴ1፥2
2፥6 ኢዮ3፥23፤ 19፥8፤ሰቆ3፥9
2፥7 ኢሳ54፥5፤ ኤር2፥2፤3፥1፤ሕዝ 16፥8፤ሆሴ5፥13
2፥8 ዑ፡13፤ዘኍ 18፥12፤ዘዳ8፥18፤ኢሳ 1፥3፤ሕዝ16፥15፤19፤ ሆሴ8፥4
2፥9 ሆሴ8፥7፤9፥2
2፥10 ኤር13፥26፤ ሕዝ16፥37፤23፥10
2፥11 ኢሳ1፥14፤ 24፥8፤ኤር7፥34፤16፥ 9፤ሆሴ3፥4፤9፥5፤ አሞ5፥21፤8፥10
2፥12 ኢሳ5፥6፤ 7፥23፤ኤር3፥1፤5፥17፤ 8፥13፤ሆሴ5፥7፤13፥8
2፥13 ዑ፡8፤ኢሳ65፥ 7፤ኤር7፥9፤44፥17፤ ሕዝ16፥17፤ሆሴ4፥6፡ 13፤8፥14፤11፥2፤13፥ 1፡6
2፥14 ሕዝ19፥13
2፥15 ዘ15፥18፤ኢሱ 7፥24፡26፤ኤር2፥22፤ ሕዝ16፥22፤28፥26፤ ሆሴ12፥9

[m]15 *አኮር ማለት ችግር ማለት ነው*

መሆኗ ተገልጿአል (ኤር 13፥26፤ ሕዝ 16፥39 ይመ)። ***ዕርቃኗን፤*** እስራኤል፣ በግብፅ ምድር በባርነትና በባዶነት ሆና እግዚአብሔር ባገኛት ጊዜ እንደ ነበረችው ማለት ነው (ከሕዝ 16፥4-8፤ ናሆ 3፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥4 ***የምንዝርና ልጆች፤*** 1፥2 ይመ። የእግዚአብሔር ልጆች ከሚለው ጋር ይነጻጸራል (1፥10፤ 11፥1)።

2፥5 ***እንጀራዬንና ውሃዬን ይሰጡኛል፤*** በኣል እህልን ለማብቀል አስፈላጊ የሆነውን ዝናብ እንደሚሰጥ ኡጋሪቲክ በተባለው ጽሑፍ ውስጥ ተጠቅሶአል። ***ሱፌንና የሐር ልብሴን፣ ዘይቴንና መጠጤን፣*** የፓሌስቲና ዋና ዋና የዕርሻ ውጤቶች ናቸው። እስራ ኤል የበረከቷን እውነተኛ ምንጭ አታውቅም። ***ውሽሞቼን፤*** ቍ 7፡10 ይመ። እንደ በኣል ያሉትን አማልክት ያመለክታል፤ አምላኪዎቹም ዕርሻቸው እንደሚለመልም ተስፋ ያደርጋሉ። ***ተከ ትዬ እሄዳለሁ፤*** ሚስቱ ሌሎች ወንዶችን ትፈልግ ነበር (ኤር 3፥2፤ ሕዝ 16፥33) ይመ።

2፥6 ***መንገዷን ... እዘጋለሁ፤*** እግዚአብሔር እስራኤልን በሞት ከመቅጣት ይልቅ (ከዘዳ 22፥21፤ ሕዝ 16፥39-40፤ ናሆ3፥5-7 ጋር ያነጻጽሩ) ተገልላ እንድትኖር ያደርጋል።

2፥7 ***ተከትላ ትሄዳለች፤*** በሆሴዕ ውስጥ የሚገኝና ከባዕድ አምልኮ ጋር የተገናኘ ቃል ሲሆን፣ በሌላ ቦታ የዕብራይስጡ ቃል “መቀጠል” ወይም “ማሳደድ” የሚል ትርጒም አለው (6፥3፤ 8፥3፤ 12፥1)። ***ትፈልጋቸዋለች፤*** 5፥6፡15 ይመ። ***አታገኛቸውም፤*** 5፥6 ይመ። ***ባሌ፤*** እግዚአብሔርን ለማለት ነው። ***እመለሳለሁ፤*** ለዚህ የተሰጠው የዕብራይስጡ ቃል ንስሓ መግባትን ያመለክታል።

2፥8 ***በኣል፤*** የከነዓናውያን አምላክ ሲሆን የአየር ሁኔ ታን፣ የእህል ምርታማነትን፣ የእንስሳት መራባትንና የሰው ልጅ መባዛትን እንደሚቈጣጠር ይታመን ነበር (የመሳ 2፥13 ማብ ይመ)። ***ብርና ወርቅን፤*** የጣዖትን ምስል ለመሥራት ይጠቀሙባ ቸው ነበር (8፥4፤ 9፥6፤ 13፥2 ይመ)። ***እኔ እንደ ሆንሁ አላወቀ ችም፤*** ከነዓናውያን እህል፣ የወይን ጠጅና ዘይት የሚሰጠን በኣል ነው ብለው ያምኑ ነበር።

2፥9 ***እወስዳለሁ፤*** እግዚአብሔር ከዕርሻ የሚገኘውን ፍሬ፣ የበጉንና የፍየሉን በረከት በመንሣት የእነዚያ በረከቶች ትክክለኛ ምንጭ ማን መሆኑ እንዲታወቅ አደረገ።

2፥10 ***ነውሯን እገልጣለሁ፤*** አመንዝራዪቱ ሚስት በአደባ ባይ ለዕፍረት ተጋለጠች (ሰቆ 1፥8፤ ሕዝ 16፥37፤ 23፥39 ይመ)። ***የሚያድናት የለም፤*** በኣል ያድናት ዘንድ ኀይል የለውም።

2፥11 ***በዓሎቿን... አስቀራለሁ፤*** በስደት ውስጥ እነዚያ የደ ስታ ወራት ትዝታ ብቻ ሆነው ይቀራሉ። ***የዓመት ... በዓሎቿ፤*** ዘፀ 23፥14-17፤ ዘዳ 16፥16 ይመ (እንዲሁም “የብሉይ ኪዳን በዓ ላትና ሌሎች የተቀደሱ ቀናት” የሚለውን ሠንጠረዥ ይመ)። ***የወር መባቻዎቿን፤*** 2ነገ 4፥23፤ ኢሳ 1፥13፤ አሞ 8፥5 ይመ። ***ሰንበቶቿን፤*** ዘፀ 20፥8-11 ይመ።

2፥12 ***ከውሽሞቼ የተቀበልሁት ዋጋ፤*** ለሴትኛ አዳሪ የሚከፈል ገንዘብ ነው 9፥1፤ ዘዳ 23፥18፤ ሕዝ 16፥33፤ ሚክ 1፥7 ይመ)። እስራኤል የእርሻ ምርቷን ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከምታመልካቸው አማልክት እንደምታገኝ ታምናለች (ዘዳ 11፥13-14 ይመ)። ***ጫካ፤*** ኢሳ 5፥5-6፤ 7፥23፤ 32፥13 ሚክ 3፥12 ይመ።

2፥13 ***ቀናት፤*** የበዓል ቀናት ማለት ነው። ***ተከትላ ሄዳ ለች፤*** የቍ 5 ማብ ይመ። ***ረስታለች፤*** በሆሴዕ ውስጥ ማወቅ ለሚለው ቃል ተቃራኒ ነው (ከ13፥4-6 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥14 ***ወደ ምድረ በዳ፤*** ዳግመኛ ቃል ኪዳን ለማድረግ ነው (ቍ 19-20 ይመ)። በከነዓን እስራኤላውያን አማልክት ለማ ምለክ ከመፈተናቸው በፊት በምድረ በዳ የተንከራተቱበትን ጊዜ ያመለክታል። ***በፍቅር ቃል አነጋግራታለሁ፤*** ማባበልና ማጽናናት በተሞላበት ሁኔታ ማለት ነው (ከዘፍ 34፥3፤ ሩት 2፥13፤ ኢሳ 40፥2 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር በፍርድ ጊዜ እንኳ ፍቅሩን ሳያቋርጥ ይገልጻል።

2፥15 ***የአኮርንም ሸለቆ፤*** በኢያሪኮ አቅራቢያ የሚገኝ ነው (ኢሱ 7፥1-26፤ 15፥7፤ ኢሳ 65፥10 ይመ)። ነቢዩ የልጆቹን ስም ትርጒም እንደለወጠ ሁሉ፣ የአኮርንም ትርጒም ለውጦአል (አግ ራጌ ትርጒም ይመ)፤ ሸለቆው፣ በተስፋይቱ ምድር እግዚአብሔር በመጀመሪያ ፍርዱን በሕዝቡ ላይ የገለጠበት ቦታ ሲሆን፣ አሁን የአዲስ ተስፋ ምልክት ሆኖ ተጠቅሶአል።

እንደ ልጅነቷም ጊዜ ትዘምራለች።[ሠ]”
16“በዚያ ቀን፣ ‘ባሌ’ ብለሽ፣
ትጠሪኛለሽ”
ይላል *እግዚአብሔር*፤
“ከእንግዲህም፣ ‘ጌታዬ’[ረ] ብለሽ
አትጠሪኝም።
17የበኣል አማልክትን ስም ከአንደበቷ
አስወግዳለሁ፤
ከእንግዲህም ስሞቻቸው አይነሡም።
18በዚያን ቀን ከምድር አራዊትና ከሰማይ
ወፎች፣
በምድርም ላይ ከሚንቀሳቀሱ ፍጥረት
ጋር፣
ቃል ኪዳን አደርግላቸዋለሁ፤
ሁሉም በሰላም እንዲኖሩ፣
ቀስትን፣ ሰይፍንና ጦርነትን፣
ከምድሪቱ አስወግዳለሁ።
19ለእኔ እንድትሆኚ ለዘላለም አጭሻለሁ፤
በጽድቅና በፍትሕ፣
በፍቅርና በርኅራኄም አጭሻለሁ።
20በታማኝነት አጭሻለሁ፤
አንቺም *እግዚአብሔርን* ታውቂያለሽ።

21*እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
“በዚያ ቀን እኔ እመልሳለሁ፤
ለሰማያት እመልሳለሁ፤
እነርሱም ለምድር ምላሽ ይሰጣሉ፤
22ምድርም ለእህል፣
ለአዲስ የወይን ጠጅና ለዘይት ምላሽ
ትሰጣለች፤
እነርሱም ለኢይዝራኤል[ሰ] ምላሽ
ይሰጣሉ።
23ስለ ራሴ ስል በምድሪቱ እተክላታለሁ፤
‘ምሕረትን ያላገኘ’[ሸ] ብዬ የጠራሁትንም
እምረዋለሁ፤
‘ሕዝቤ አይደላችሁም’[ቀ] ተብለው
የተጠሩትንም፣ ‘ሕዝቤ’ እላቸዋለሁ፤
እነርሱም፣ ‘አንተ አምላኬ ነህ’
ይላሉ።”

## የሆሴዕ ከሚስቱ ጋር መታረቅ

3 *እግዚአብሔር* እንዲህ አለኝ፤ “እርሷ
በሌላ ሰው የምትወደድ አመንዝራ ብት
ሆንም፣ አሁንም ሂድና ሚስትህን ውደ
ዳት፤ ወደ ሌሎች አማልክት ዞወር ቢሉና
ለእነርሱም የተቀደሰውን የዘቢብ ጥፍጥፍ
ቢወዱም፣ *እግዚአብሔር* እስራኤላውያንን
እንደ ወደዳቸው አንተም እርሷን ውደዳት።”
2ስለዚህ በዐሥራ አምስት ሰቅል ጥሬ
ብርና በአንድ ቆሮስ ተኩል መስፈሪያ ገብስ
ገዛኋት። 3እኔም፣ “ከእኔ ጋር ብዙ ቀን
ተቀመጪ፤[በ] አታመንዝሪ ወይም ሌላ ሰው
አትውደጂ፤ እኔም ከአንቺ ጋር እኖራለሁ”
ብዬ ነገርኋት።
4እስራኤላውያን ለብዙ ዘመን ያለ ንጉ
ሥና ያለ አለቃ፣ ያለ መሥዋዕትና ያለ ዐምደ
ባዕት፣ ያለ ኤፉድና ያለ ባዕት ምስል

2፥16 ኢሳ54፥5
2፥17 ዘ23፥13፤ኢሱ 23፥7፤መዝ16፥4፤ ዘካ13፥2
2፥18 ኢዮ5፥22፡ 23፤መዝ46፥9፤ኢሳ 2፥4፤ኤር23፥6፤ሕዝ 34፥25፤ዘካ9፥10
2፥19 ኢሳ1፥27፤ 54፥8፤62፥4፤ 2ቆሮ11፥2
2፥20 ኤር31፥34፤ ሆሴ4፥1፤6፥6፤13፥4፤ ሕዝ16፥8
2፥21 ኢሳ55፥10፤ ዘካ8፥12፤ሚል3፥ 10-11
2፥22 ኤር31፥12፤ ሕዝ36፥2930፤ሆሴ 1፥4፤14፥7፤ኢል2፥19
2፥23 ቍ1፤ኢሳ19፥ 25፤ኤር29፥12፤31፥ 27፤ሆሴ1፥6፡10፤ሮሜ 9፥25፤1ጴጥ2፥10
3፥1 2ሳሙ6፥19፤ ሆሴ1፥2
3፥4 ዘ25፥7፤መሳ 17፥56፤18፥1417፤ስ ቆ2፥9፤ዳን11፥31፤ሆሰ 2፥11፤10፥1፤13፥11፤ ዘካ10፥2

[ሠ]15 ወይም *ትሆናለች*
[ረ]16 ዕብራይስጡ *በኣል* ይላል
[ሰ]22 *ኢይዝራኤል ማለት እግዚአብሔር ይተክላል ማለት ነው*
[ሸ]23 ዕብራይስጡ *ሎሩሃማ* ይላል
[ቀ]23 ዕብራይስጡ *ሎዓሚ* ይላል
[በ]3 ወይም *ቆዪ*

2፥16-17 *ባሌ... ጌታዬ... የበኣል፤* ድምፁቱ አንድ ሆኖ የተለያየ ትርጕም ያለውን ቃል የሚያመለክት ኅብር አገላለጽ ነው፤ “ባሌ” ለሚለው ከተሰጡት ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት መካከል አንዱ (“ጌታዬ”) “በኣል” ከሚባለው የጣዖት አምላክ ስም ጋር ይመሳሰላል (የቍ 16 አማራጭ ትር ጕም ይመ)። “ጌታ” ለሚለው የቆመው የዕብራይስጥ ቃል ለእግዚአብሔር መጠ ሪያነት ከቶ እንዳይውል እስከሚደረግ ድረስ በከፍተኛ ደረጃ ይጠላል።

2፥18 *ቃል ኪዳን አደርግላቸዋለሁ፤* 6፥7፤8፥1 ይመ። በቍ12 ላይ የተጠቀሱት አጥፊ እንስሳት እንደዚሁም ወፎችና በመሬት ላይ የሚንቀሳቀሱት ነፍሳት ከእንግዲህ ወዲህ ለሕይ ወት አስፈሪ አይሆኑም። ተፈጥሮና ታሪክ በሰላም ይጣመራሉ (ኢሳ 11፥6-9፤ 65፥25 ይመ)። *በሰላም እንዲኖሩ፤* ኤር 33፥16፤ ሕዝ 34፥24-28 ይመ። *ቀስትን፣ ሰይፍንና፤* 1፥5 ይመ። ጦርነትም አብቅቶአል። *ከምድሪቱ፤* የእስራኤል ምድር ማለት ነው (1፥2፤ 4፥1፡3፤ 9፥3፤ 10፥1 ይመ)።

*2፥19-20፤* በዚህ ክፍል የተጠቀሱት አምስት በጎ ምግባ ራት፣ በቃል ኪዳን መተጫጨት ከሚከፈል ገንዘብ ይልቅ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው (ዘፀ 22፥16-17፤ ዘዳ 22፥23-29፤ 1ሳሙ 18፥25፤ 2ሳሙ 3፥14 ይመ)።

2፥19 *በጽድቅና፤* 10፥12፤ ኤር 23፥6፤ አሞ 6፥12፤ ሚክ 6፥5 ይመ። *በፍትሕ፤* አሞ 5፥24 ይመ። *በፍቅርና፤* 4፥1፤ 6፥4፤ 10፥12፤ 12፥6 ይመ። *በርኅራኄም፤* እግዚአብሔር ሊያደርገው ካሰበው ክፉ ነገር መመለሱን ያመለክታል (1፥6 እና አማራጭ ትርጕሙን ይመ)። “ሎሩሃማ” በቁሙ ርኅራኄ መንሣት ማለት ነው (ከመዝ 51፥1፤ 103፥3-14 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥20 *በታማኝነት፤* እምነት የሚጣልበት ማለት ነው (ዘዳ 32፥4፤ መዝ 88፥11 ይመ)። *ታውቂያለሽ፤* የዕብራይስጡ ቃል በጣም የጠበቀ የጋብቻ ግንኙነትን ያመለክታል (ዘፍ 19፥8፤ ዘኍ 31፥17-18፡35)፤ በተጨማሪም በኪዳን የተጉዳኙ ፍቅረኞችን ጥብቅ ትውውቅ ያሳያል (4፥1፡6፤ 5፥4፤ 6፥3፡6፤ 8፥2፤11፥3፤ 13፥4 ይመ)።

2፥22 *ለኢይዝራኤል፤* እዚህ ላይ ቃሉ እግዚአብሔር ይተ ክላል የሚለውን ለማመልከት ገብቶአል (አማራጭ ትርጕሙንና ቍ 23 እንዲሁም የ1፥11 ማብ ይመ)። በልጆቹ ስም የተገለጸው መርገም ወደ በረከት ተለውጦአል (1፥10 ይመ)። የቃል ኪዳ ኑም ሐሳብ እንዲህ ይላል፤ “የራሴም ሕዝብ አደርጋችኋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ” (ዘፀ 6፥7፤ ዘካ 8፥8 ማብ ይመ)።

2፥23 *አንተ አምላኬ ነህ፤* ሕዝቡ እግዚአብሔር ላደረገው ምሕረት ምላሽ ይሰጣሉ፤ ይህ ጥቅስ አሕዛብ ወደ ቤተ ክርስቲ ያን መምጣታቸውን ለማመልከት በሮሜ 9፥25፤ 1ጴጥ 2፥10 ላይ በከፊል ተጠቅሶአል።

3፥1 *እንዲህ አለኝ፤* ምዕራፍ ሦስት የተተረከው በአንደኛ መደብ ሲሆን፣ ምዕራፍ አንድ ግን በሦስተኛ መደብ ነበር። *ሂድና ሚስትህን ውደዳት፤* ሆሴዕ ለጋለሞታዪቱ ጎሜር የነ በረው ፍቅር፣ እግዚአብሔር ለአመንዝራዪቱ እስራኤል ያለውን ፍቅር ይገልጻል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ፍቅር (11፥1፤ 14፥4 ይመ) የመጽሐፉ መሪ ሐሳብ ነው። *ሌሎች አማልክት፤* ዘፀ 20፥3፤ ዘዳ 31፥20 ይመ። *የዘቢብ ጥፍጥፍ፤* ስለ አዝመራ ቸው በኣልን ለማመስገን የሚያቀርቡለት ስጦታ ነው።

*3፥2፤* ጎሜር በእርግጥ ባሪያ ሆነች፤ ሆሴዕም መልሶ ገዛት። *ዐሥራ አምስት ሰቅል፤* ባሪያን ለመግዛት (ዘፀ 21፥7፡32) ወይም በስእለት የተሰጠችን ሴት (ዘሌ 27፥4) ነጻ ለማውጣት ከተመደ በው ገንዘብ ግማሽ ማለት ነው።

*3፥3-5፤* ተግርኮ መሄድንና ከምርኮ መመለስን ያመለክታል።

3፥3 *ብዙ ቀን፤* ለዘላለም ማለት አይደለም። *ተቀመጪ፤* ተለይታ እንደ ነበረ ያመለክታል (አማራጭ ትርጕሙንና 2፥6 ይመ)፤ ይህም ከእስራኤል ምርኮ ጋር የሚነጻጸር ነው።

3፥4 *ንጉሥና፤* 1፥4፤ 5፥1፤ 8፥4፡10፤ 10፥15፤ 13፥10-11 ይመ። *አለቃ፤* 5፥10፤ 7፥3፡5፤ 8፥4፤ 13፥10 ይመ። *ያለ መሥ ዋዕትና፤* 6፥6፤ 8፥11፡13 ይመ። *ዐምደ ባዕት፤* 10፥1-2፤ ዘዳ 16፥22፤ 1ነገ 14፥23፤ 2ነገ 17፥10፤ ሚክ 5፥13 ይመ። *ኤፉ ድና፤* እዚህ ላይ ከጣዖት ጋር የተያያዘ ምስል ነው (መሳ 8፥27፤ 17፥5 ይመ)። *ጣዖት፤* ዘፍ 31፥30፤ 1ሳሙ 19፥13፡16 ይመ።

ይኖራሉና:: 5ከዚያ በኋላ እስራኤላውያን
ተመልሰው አምላካቸውን እግዚአብሔርንና ንጉ
ሣቸውን ዳዊትን ይፈልጋሉ፤ በመጨረሻ
ውም ዘመን በመንቀጥቀጥ ወደ እግዚአብሔ
ርና ወደ በረከቱ ይመጣሉ::

## በእስራኤል ላይ የቀረበ ክስ

4 በምድሪቱ በምትኖሩ በእናንተ ላይ
እግዚአብሔር የሚያቀርበው ክስ
ስላለው፣
እናንት እስራኤላውያን ይህን
የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤
"ታማኝነት የለም፤ ፍቅርም የለም፤
እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድሪቱ የለም::
2በዚያ ያለው ርግማን፣⁺ መዋሸት፣
መግደል፣
መስረቅና ማመንዘር ብቻ ነው፤
ቃል ኪዳንን ሁሉ ያፈርሳሉ፤
ደም ማፍሰስና ግድያ ይበዛል::
3ስለዚህ ምድሪቱ አለቀሰች፣‡
በውስጧም የሚኖሩ ሁሉ ኰሰመኑ፤
የምድር አራዊት፣ የሰማይ ወፎች፣
የባሕርም ዓሦች አለቁ::

4"ነገር ግን ማንም ሰው አይከራከር፤
ማንም ሌላውን አይወንጅል፤
በካህናት ላይ ክስን እንደሚያቀርቡ፣
ሕዝብህ እንደዚያው ናቸውና::
5ቀንና ሌሊት ትደናበራላችሁ፤
ነቢያትም ከእናንተ ጋር ይደናበራሉ፤
ስለዚህ እናታችሁን አጠፋታለሁ፤
6ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ
ጠፍቶአል::
"ዕውቀትን ስለናቃችሁ፣
እኔም ካህናት እንዳትሆኑ ናቅኋችሁ፤
የአምላካችሁን ሕግ ስለ ረሳችሁ፣
እኔም ልጆቻችሁን እረሳለሁ::
7ካህናት በበዙ ቍጥር፣
በእኔ ላይ የሚያደርጉት ኀጢአት
በዝቶአል፤
ክብራቸውንም⌜ በውርደት ለውጠዋል::⌝
8የሕዝቤ ኀጢአት ለመብል ሆኖላቸዋል፤
ርኵሰታቸውንም እጅግ ወደዱ::
9ካህናትም ከሕዝቡ የተለዩ አይደሉም፤
ሁሉንም እንደ መንገዳቸው
እቀጣቸዋለሁ፤
እንደ ሥራቸውም እከፍላቸዋለሁ::

10"ይበላሉ ግን አይጠግቡም፤
ያመነዝራሉ ግን አይበዙም፤
እግዚአብሔርን በመተው፣
ራሳቸውን 11ለአመንዝራነት፣
ለአሮጌና ለአዲስ የወይን ጠጅ አሳልፈው

3፥5 ዘዳ4፥29:30፤ 1ሳሙ13፥14፤መዝ 18፥45፤ኢሳ9፥13፤ 10፥20፤ኤር50፥45፤ ሆሴ5፥15፤11፥10፤ ሚክ4፥12
4፥1 ኢዮ10፥2፤ ምሳ10፥21፤24፥2፤ ኢሳ1፥3፤ኤር2፥9፤7፥ 28፤51፥5፤ሆሴ2፥ 20፤ኢል1፥2:14
4፥2 2ነገ21፥16፤ ኢሳ1፥15፤59፥3፤ኤር 9፥2፤ሕዝ22፥2:9፤ሆሴ 5፥2፤6፥9፤7፥1:3፤ 10፥4:13፤11፥12
4፥3 ኢሳ15፥6፤ 33፥9፤ኤር4፥25:28፤ 9፥10፤ሕዝ38፥20፤ ሶፎ1፥3
4፥4 ዘዳ17፥12፤ ሕዝ3፥26
4፥5 ሕዝ7፥19፤ 14፥7፤ሆሴ2፥2
4፥6 ምሳ10፥21፤ ኢሳ1፥3፤ሆሴ2፥13፤ 8፥1:12፤ሚል2፥78
4፥7 ሆሴ9፥11፤ 10፥1:6፤13፥6፤ዕን 2፥16
4፥8 ኢሳ56፥11፤ ሆሴ14፥1፤ሚክ3፥11
4፥9 ኢሳ24፥2፤ኤር 5፥31፤ሆሴ8፥13፤9፥9: 15፤10፥10፤12፥2

⁺2 መርገምን ያመለክታል
‡3 ወይም ደረቀች
⌜7 ማሶሬቲክ የሚለው እንዲሁ ሲሆን የጥንት ዕብራውያን ጸሐ ፍት ትውፊት ግን ክብሬን ይላል
⌝7 ሱርስትና የጥንት ዕብራውያን ጸሐፍት ትውፊት የሚሉት እንዲሁ ሲሆን ማሶሬቲክ ግን እለውጠዋለሁ ይላል

3፥5 *ተመልሰው፤* ሆሴዕ ከተናገረው ውስጥ ይህ ቍልፍ ቃል ነው (2፥7፤ 5፥4፤ 6፥1፤ 7፥10፤ 11፥5፤ 12፥6፤ 14፥1-2 ይመ):: *ይፈልጋሉ፤* እስራኤል ንስሓ እንደምትገባ ያሳያል (ከ5፥15 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም አሁን ከያዘችው የደነደነ ልብና ዐመፅ ጋር የሚቃረን ነው (7፥10):: *አምላካቸውን እግዚአብሔርን፤* 12፥9፤ 13፥4፤ ኤር 50፥4 ይመ:: *ንጉሣቸውን ዳዊትን፤* ከዳዊት ሥርወ መንግሥት የሆነውን መሲሕ ያመለክታል (ኤር 30፥9፤ ሕዝ 34፥24 ይመ):: ከሰሎሞን ሞት በኋላ የሰሜኑ መንግሥት ከዳዊት ቤት የሆነ ንጉሥ አላነገሠችም:: *በረከቱ፤* የተወሰደባትን የወይን አትክልትና የወይራ ዛፎችን (2፥12-13:21 ይመ) እንዲሁም የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነውን ሁሉ ያመለክታል (ኤር 31፥12-14 ይመ):: *በመጨረሻውም ዘመን፤* በብሉይ ኪዳን ይህ ሐረግ በዕብራይስጡ ዐሥራ ሦስት ጊዜ ተጠቅሶአል፤ አንዳንዴ የወደ ፊቱን ወይም መጪውን ጊዜ (ዘፍ 49፥1) የሚያመለክት ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ ግን (እዚህ ላይ እንዳለው) ከመሲሑ ልደት እስከ ዳግም ምጽአቱ ያለውን ዘመን ያመለክታል (ኢል 2፥28 ይመ፤ ከሐሥ 2፥17፤ ዕብ 1፥2 ጋር ያነጻጽሩ)::

*4፥1-14፥9፤* እስራኤል የከነዓናውያንን ሃይማኖት መከተሏንና የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፏን እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ተንኰሏን በስፋት የሚያስረዳ ክፍል ነው::

4፥1 *ክስ፤* ሆሴዕ የእግዚአብሔር አፍ በመሆን፣ ታማኝ ባልሆነችውና ቃል ኪዳን ባፈረሰችው እስራኤል ላይ ክስ ይመሠርታል (ከቍ 4፤ ኢሳ 3፥13፤ ኤር 2፥9፤ ሚክ 6፥2 ጋር ያነጻጽሩ):: *ቃል ስሙ፤* ኢሳ 1፥10፤ ኤር 2፥4፤ ሕዝ 6፥3 ይመ:: *ታማኝነት፤* ቃል ኪዳኑን ለሚጠብቅ አምላክ ታማኝ መሆንና (ኢሱ 24፥14) ትክክለኛ የሆነውን ነገር ለሰዎች ማድረግ ነው (ምሳ 3፥3):: *ፍቅርም፤* 2፥19፤10፥12 ይመ:: *እግዚአብሔርንም ማወቅ፤* 2፥20 እና ማብ እንዲሁም 5፥4፤6፥6 ይመ::

4፥2 *ርግማን... ማመንዘር፤* ዐሥርቱ ትእዛዛትን በመተላለፍ (ዘፀ 20፥13-16፤ ዘዳ 5፥17-20 ይመ) የተሠሩ ኀጢአቶች ተዘርዝረዋል፤ በኤር 7፥9 ላይ ካለው ጋር ይመሳሰላል:: *ደም ማፍሰስ፤* (1) ግድያን (6፥8-9 ይመ)፤ (2) ከዳግማዊ ኢዮርብዓም ሞት በኋላ ሦስት ነገሥታት በአንድ ዓመት በነገሡ ጊዜ (2ነገ 15፥10-14) የተፈጸሙትን የነገሥታት ግድያዎች እንዲሁም (3) ለጣዖት መሥዋዕት እንዲሆን የተገደሉትን ሰዎች (መዝ 106፥38፤ ሕዝ 16፥20-21፤ 23፥37) ሁሉ ያካትታል:: እግዚአብሔርን መፍራት በሌለበት ቦታ (ቍ1) መልካም ግብረ ገብ አይኖርም::

4፥3 *ምድሪቱ አለቀሰች፤* እግዚአብሔር በሰው ኀጢያት ላይ የሚሰጠው ፍርድ በምድር ላይ ያሉትን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ የሚነካ ነው (ኢሳ 24፥3-6፤ ኤር 4፥23-28 ይመ):: *ኰሰመኑ፤* ኢሳ 19፥8፤ ኤር 14፥2፤ 15፥9፤ ኢል 1፥10 ይመ::

*4፥4-9፤* የእግዚአብሔርን ሕግ የመጠበቅና መንፈሳዊ ምሪትን የመስጠት ኀላፊነት (ዘዳ 31፥9-13፤ 33፥10፤ 2ዜና 17፥8-9፤ ዕዝ 7፥6:10፤ ኤር 18፥18 ይመ) ባለባቸው ካህናት ላይ የቀረበ ክስ ነው:: በምድሪቱ ላይ ለሚደርሰው የእግዚአብሔር ፍርድና ቍጣ ካህናት ሕዝቡን ተጠያቂ በማድረግ እንዳይከሱ ሆሴዕ ያስጠነቅቃል፤ ምክንያቱም ካህናቱ ራሳቸው ጥፋተኞች ስለ ሆኑ ሕዝቡ መልሶ እነርሱን ሊከስ ይችላልና (ቍ9፤ ኢሳ 28፥7፤ ኤር 2፥26፤ 4፥9፤23፥11 ይመ)::

4፥5 *ትደናበራላችሁ፤* 5፥5 ይመ:: *ነቢያትም፤* ሚክ 2፥6: 11፤ 3፥5-7 ይመ:: *እናታችሁን፤* አገሪቱን ማለት ነው (2፥2:5፤ ኢሳ 50፥1 ይመ)::

4፥6 *ሕዝቤ፤* እስራኤልን ነው (ቍ 8:12፤ 2፥1:23፤ 6፥11፤ 11፥7፤ ሚክ 6፥3 ይመ):: *ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል፤* ይህ ሊሆን የቻለው ካህናቱ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ስላላስተማሩ ነው:: *ዕውቀትን ስለ ናቃችሁ... ናቅኋችሁ፤* አጸፋዊ ቅጣትን ያመለክታል:: *የአምላካችሁን ሕግ፣* ካህናት በታማኝነት ሊፈጽሙትና ለሌሎችም ሊያስተላልፉት የሚገባቸውን፣ ለእስራኤልም ሕይወት የሆነውን (ዘዳ 32፥47 ይመ) የእግዚአብሔርን ቃል ያመለክታል::

4፥7 *ክብራቸውንም፤* እግዚአብሔርን ነው (መዝ 106፥20 ይመ)::

4፥8 *ኀጢአት ለመብል ሆኖላቸዋል፤* ኀጢአቱ እንዳይስፋፋ ከመግታት ይልቅ መቀጠሉ ጠቅሞአቸዋል (8፥13 ይመ)፤ ምክንያቱም ካህናቱ ለመሥዋዕት የቀረበውን ሁሉ ሙልጭ አድርገው ይበሉ ነበር (1ሳሙ 2፥13-17)::

4፥9 *ካህናትም ከሕዝቡ የተለዩ አይደሉም፤* አንድም ሰው ሳይቀር ሁሉም ስለ ሠሩት ኀጢአት ይቀጣሉ::

4፥10 *ይበላሉ ግን አይጠግቡም፤* ለተሠራው ኀጢአት ተገቢ የሆነ ቅጣት ነው:: *ያመነዝራሉ፤* ቍ 12:18፤ 2፥4፤ 6፥10፤ 9፥1፤ መዝ 106፥39 ይመ:: ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ከመስጠት ይልቅ ለምንዝርና አሳልፈው ሰጡ::

4፥11 *ለአሮጌ... ወይን ጠጅ፤* 7፥5፤ 9፥10፤ 14፥7 ይመ::

ስጡ፤
በእነዚህም [12]የሕዝቤ ማስተዋል ተወሰደ፤
ከዕንጨት የተሠራውን ጣዖት ምክር
ይጠይቃሉ፤
ዘንጋቸውም ይመልስላቸዋል።
የአመንዝራነት መንፈስ ያስታቸዋል፤
ለአምላካቸውም ታማኝ አልሆኑም።
[13]በተራሮችም ጫፍ ላይ ይሠዋሉ፤
መልካም ጥላ ባለው፣ በባሉጥ፣
በኮምቦልና በአሆማ ዛፍ ሥር፣
በኰረብቶችም ላይ የሚቃጠል ቍርባን
ያቀርባሉ።
ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁ ዘማዊ፣
ምራቶቻችሁም አመንዝራ ይሆናሉ።

[14]"ሴቶች ልጆቻችሁ ዘማውያን ሲሆኑ፣
የልጆቻችሁም ሚስቶች ሲያመነዝሩ
አልቀጣቸውም።
ወንዶች ከጋለሞቶች ጋር ይሴስናሉ፤
ከቤተ ጣዖት ዘማውያን ጋር ይሠዋሉና፤
የማያስተውል ሕዝብ ወደ ጥፋት
ይሄዳል!

[15]"እስራኤል ሆይ፤ አንቺ ብታመነዝሪም፣
ይሁዳ በበደለኛነት አትጠየቅ።

"ወደ ጌልገላ አትሂዱ፤
ወደ ቤትአዌንም[1] አትውጡ፤
'ሕያው እግዚአብሔርን' ብላችሁም
አትማሉ።

[16]እስራኤላውያን እንደ እልኸኛ ጊደር፣
እልኸኞች ናቸው፤
ታዲያ እግዚአብሔር እነርሱን በመልካም
መስክ ውስጥ እንዳሉ የበግ ጠቦቶች
እንዴት ያሰማራቸዋል?
[17]ኤፍሬም ከጣዖት ጋር ተጣምሯል፤
እስቲ ተውት፤
[18]መጠጣቸው ባለቀ ጊዜ እንኳ፣
ዘማዊነታቸውን አያቆሙም፤
ገዦቻቸውም ነውርን አጥብቀው
ይወዳሉ።
[19]ዐውሎ ነፋስ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል፤
መሥዋዕቶቻቸውም ኀፍረት
ያመጡባቸዋል።

## በእስራኤል ላይ የተነገረ ፍርድ

5 "እናንተ ካህናት፤ ይህን ስሙ!
እናንተ እስራኤላውያን፤ አስተውሉ!
የንጉሥ ቤት ሆይ፤ ስሙ!
ይህ ፍርድ በእናንተ ላይ ነው፤
በምጽጳ ወጥመድ፣
በታቦርም ላይ የተዘረጋ መረብ
ሆናችኋልና።
[2]ዐመፀኞች በግድያ በርትተዋል፤
ሁሉንም እቀጣቸዋለሁ።
[3]ስለ ኤፍሬም ሁሉን ዐውቃለሁ፤

4፥12 መዝ73፥27
4፥13 ኢሳ1፥29፤ ኤር2፥20፤3፥6፤ሆሴ 2፥13፤10፥8፤11፥2፤ አሞ7፥17
4፥14 ቍ 11፥19፤ ዘፍ38፥21፤ምሳ10፥2 1፤ሆሴ9፥10
4፥15 ኢሱ7፥2፤ ኤር4፥2፤ሆሴ5፥8፤ 9፥15፤12፥11፤ አሞ4፥4፤5፥5
4፥16 ዘ32፥9፤ኢሳ 5፥17፤7፥25፤ ኤር31፥18
4፥19 ቍ 13፥14፤ኢሳ 1፥29፤ሆሴ12፥11 13፥15
5፥1 ኢዮ10፥2፤ ኤር5፥26፤ሆሴ6፥9፤ 9፥8
5፥2 ሆሴ4፥2፤9፥15
5፥3 ሕዝ23፥7፤ ሆሴ1፥2፤6፥10፤ አሞ5፥12

[1]15 ቤትአዌን የእግዚአብሔር ቤት የተባለችው ቤቴል ስትሆን፣ የቃሉ ትርጉም የክፋት ቤት ማለት ነው

ለአዲስ፤ 2፥8-9፡22፤ 7፥14፤ 9፥2 ይመ።

4፥12 *ከዕንጨት የተሠራውን ጣዖት፤* የጣዖት አምላክ ምስል ነው (ኤር 2፥27፤ 10፥8፤ ዕን 2፥19 ይመ)። *ዘንጋቸው፤* ከዕንጨት የተሠራ ጣዖት ወይም የጠንቋይ በትር ነው (ሕዝ 21፥21 ይመ)። *የአመንዝራነት መንፈስ፤* 5፥4 ይመ። መንፈስ ከሚለው አንጻር፣ የዕብራይስጡ ዘይቤያዊ አባባሉ የውስጥ ዝንባሌን ይገልጻሉ።

4፥13 *ይሠዋሉ፣* 8፥13 ይመ። *በተራሮችም ጫፍ፤ ጣዖት* አምላኪዎች መሠዊያን ለመሥራት የሚመርጡት ቦታ ነው (10፥8፤ ዘዳ 12፥2፤ 1ነገ 14፥23፤ 2ነገ 17፥10፤ ኤር 2፥20፤ 3፥6 ይመ)። ከኡጋሪት የተገኙት የፅሑፍ ሰሌዳዎች፣ ከከነዓናውያን ልጅ መውለድ ሲፈልጉ የአምልኮ ሥርዐት ለመፈጸም ወደ ማምለኪያ ኰረብታዎች ይጓዙ እንደ ነበር ይገልጻሉ። *በባሉጥ ... በአሆማ፣* በጥላቸው ምክንያት የታወቁ ዛፎች ናቸው። *አመንዝራ ይሆናሉ፤* ከነዓናውያን ልጅ ለማግኘት የሚያደርጉት ሥርዐተ አምልኮ፣ ከሥነ ምግባር ውጭ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምንም (ቍ 14) የሚያካትት ነበር።

4፥14 *አልቀጣቸውም፤* ወንዶች፣ ሚስቶቻቸው ስለሚፈጽሙት ሥነ ምግባር የጐደለው ነገር ይቀጧቸዋል፤ እግዚአብሔር ግን በግብዞች የሚፈጽሙትን ቅጣት አይተባበርም። *ጋለሞቶች፤* ዝሙት አዳሪዎችን ሁሉ ያመለክታል ዘፍ (34፥31፤ ዘሌ 21፥14፤ ሕዝ 16፥31 ይመ)። *ከቤተ ጣዖት ዘማውያን፤* ከወንዶች ጋር ዝሙት በመፈጸም በቤተ ጣዖት ውስጥ የሚያገለግሉ ሴቶች ናቸው (ከዘፍ 38፥21-22፤ ዘዳ 23፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። *የማያስተውል፤* ከ14፥9 ጋር ያነጻጽሩ።

4፥15 *ይሁዳ፤* ማስጠንቀቂያው በተለይ ይሁዳን የሚመለከት ነው (ከዚህ መጽሐፍ መግቢያ፣ "ጸሓፊውና የተጻፈበት ዘመን" የሚለውን ይመ)። *በበደለኛነት፤* 10፥2፤ 13፥1፤ 14፥1 ይመ። *አትሂዱ፤* ለሕዝቡ ሁሉ የተነገረ ነው። *ጌልገላ፤* በኢያሪኮ አቅራቢያ የሚገኝ አካባቢ ነው (9፥15፤ 12፥11፤ ኢሱ 4፥19-20፤ 1ሳሙ 11፥13-15 ይመ)፤ ይህም እስራኤላውያን የጣዖት አምልኮን የሚያካሂዱበት ቦታ ነበር። *ቤትአዌን፤* ለቤቴል የተሰጠ ምጸታዊ ስም ነው (አግራጌ ትርጕሙንና 5፥8 ይመ)። ቀዳማዊ ኢዮርብዓም ካቋቋማቸው የባዕድ አምልኮ ማዕከላት (1ነገ 12፥29) አንዱ ነው። *ሕያው እግዚአብሔርን፤* በጣም የከበረ መሐላ ነው (መሳ 8፥19፤ ሩት 3፥13፤ 1ሳሙ 14፥39፤ 26፥10፡16፤ ኤር 4፥2፤ 38፥16 ይመ)፤ እውነተኛውን አምላክ ስለ ሚጠራ በራሱ ትክክል ቢሆ ንም (ዘዳ 6፥13፤10፥20፤ ኢሱ 23፥7 ይመ)፣ እስራኤላውያን ከልብ እግዚአብሔርን የሚያከብሩ መስለው በተሳሳተ መልክ ስለ ተጠቀሙበት (ኤር 5፥2 ይመ) እዚህ ላይ ተከልክሉ ነበር።

4፥16 *እልኸኛ ጊደር፤* 10፥11፤ ኤር 2፥20 ይመ፤ ሞገደኛዋን እስራኤል የሚያመለክት ተስማሚ አገላለጽ ነው (11፥4፤ ኤር 31፥18 ይመ)። *እልኸኞች፤* ነህ 9፥29፤ ዘካ 7፥11 ይመ።

4፥17 ኤፍሬም፤ የሰሜኑ መንግሥት የሆነውን እስራኤልን ያመለክታል። *ከጣዖት፣* የወርቅ ጥጃን (8፥5፤ 13፥2፤ 1ነገ 12፥28) እንዲሁም የበኣል አምልኮዎችን (2፥8፡13) ሁሉ ያመለክታል። *ተውት፤* ምንም ርዳታ ሊያደርግለት አልቻለም (2ሳሙ 16፥11፤ 2ነገ 23፥18 ይመ)።

4፥19 *ዐውሎ ነፋስ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል፤* ቃል በቃል ሲተ ረጐም ነፋሱ በክንፉ ይሸከማቸዋል ማለት ነው። በድንገት ስደት የሚያስከትል ዐመፅን የሚያሳይ ከእህል መውቂያ ዐውድማ የተወ ሰደ (13፥3፤ መዝ 1፥4 ይመ) ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል። በዕ ብራይስጥ "ነፋስ" እና "መንፈስ" አንድ ስለ ሆኑ የዘማዊነት መንፈስ (ቍ 12፤ 5፥4) ለማለት የገባ ኅብር አገላለጽ ሊሆን ይችላል። *ኀፍረት፤* መሥዋዕት በማቅረባቸው ይሳካልናል ብለው ተስፋ አደረጉ፤ ነገር ግን ጣዖት በማምለካቸው እግዚአብሔር የሚያመጣባቸው ቅጣት በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ ለኀፍረት ይዳርጋ ቸዋል (10፥6 ይመ)።

5፥1 *ካህናት... እስራኤላውያን... የንጉሥ ቤት፣* እዚህ ላይ መልእክቱ ያተኮረባቸው ሦስቱም ክፍሎች፣ ፍትሕን የመጠበቅ ኀላፊነት ስለ ነበረባቸው ነው፤ ነገር ግን ፍርዱ በእጃቸው ተዛባ። *ወጥመድ ... መረብ፤* እንስሳትንና አዕዋፍን ለማጥመድ የሚያገለ ግሉ መሣሪያዎች ሲሆኑ፣ እዚህ ላይ ግን ኢኮኖሚንና ሕግን ተገን አድርገው በንጹሐን ላይ በመነገድ የራሳቸውን ጥቅም የሚገነቡትን ሰዎች ለማመልከት የገባ ተለዋጭ ዘይቤ ነው (ኢዮ 18፥8-10፤ መዝ 140፥5፤ ምሳ 29፥5፤ ሰቆ 1፥13 ይመ)። *ምጽጳ፤* ከዮርዳኖስ በስተ ምሥ ራቅ በገለዓድ ያለው ምጽጳ (ዘፍ 31፥43-49) ወይም በብንያም ምድር ያለው ምጽጳ (1ሳሙ 7፥5-6፤10፥17) ሊሆን ይችላል። *ታቦር፤* በኢዝራኤል ሸለቆ ደቡብ ምሥራቅ ጫፍ የሚገኝ ተራራ ነው። ይህም የእስራኤልን ውድቀት የሚገልጹ የታወቁ ድርጊቶችን በሚመለከት የሚነገር መሆን አለበት።

5፥2 *እቀጣቸዋለሁ፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማረም የሚወስደውን እርምጃ አስመልክቶ ነቢያት ደጋግመው የተናገሩት ዐቢይ ቃል ነው (ኢሳ 26፥16፤ ኤር 2፥30፤ 5፥3፤ 7፥28 ይመ)።

5፥3 *ኤፍሬም፤* የሰሜኑን መንግሥት እስራኤልን የሚያመ

እስራኤልም ከእኔ የተሰወረች
አይደለችም፤
ኤፍሬም፣ አንተ አሁን አመንዝረሃል፤
እስራኤልም ረክሳለች።
4"የሠሩት ሥራ፣ ወደ ስምላካቸው እንዲ
መለሱ አይፈቅድላቸውም፤
የአመንዝራነት መንፈስ በልባቸው አለ፤
እግዚአብሔርንም አያውቁትም።
5የእስራኤል ትዕቢት በራሷ ላይ ይመሰክራል፤
እስራኤላውያንና ኤፍሬምም
በኀጢአታቸው ይሰናከላሉ፤
ይሁዳም ደግሞ አብሮአቸው ይሰናከላል።
6እግዚአብሔርን ለመሻት፣
የበግና የፍየል መንጋ እንዲሁም የቀንድ
ከብቶቻቸውን ነድተው ሲሄዱ፣
እርሱ ስለ ተለያቸው፣
ሊያገኙት አይችሉም።
7ለእግዚአብሔር ታማኞች አልሆኑም፤
ዲቃሎች ወልደዋልና፤
ስለዚህ የወር መባቻ በዓላቸው፣
እነርሱንና ዕርሻቸውን ያጠፋል።

8"በጊብዓ መለከትን፣
በራማ እንቢልታን ንፉ፤
በቤትአዌን የማስጠንቀቂያ ድምፅ አሰሙ፤
'ብንያም ሆይ፤ መጡብህ!' በሉ።
9በቅጣት ቀን፣
ኤፍሬም ባድማ ይሆናል፣
በእስራኤል ነገዶች መካከል፣
በእርግጥ የሚሆነውን ዐውጃለሁ።
10የይሁዳ መሪዎች፣
የወሰን ድንጋዮችን እንደሚነቅሉ ሰዎች
ናቸው፤
እንደ ጐርፍ ውሃ፣
ቍጣዬን በላያቸው ላይ አፈስሳለሁ።
11ጣዖትን መከተል በመውደዱ፣[a]
ኤፍሬም ተጨቍኖአል፤
በፍርድም ተረግጦአል።
12እኔ ለኤፍሬም እንደ ብል፣
ለይሁዳም ሕዝብ እንደ ነቀዝ ሆኛለሁ።

13"ኤፍሬም ሕመሙን፣
ይሁዳም ቍስሉን ባየ ጊዜ፣
ኤፍሬም ወደ አሦር ሄደ፤
ርዳታ ለመጠየቅ ወደ ታላቁ ንጉሥ
መልእክተኛ ላከ፤
እርሱ ግን ሊያድናችሁ፣
ቍስላችሁንም ሊፈውስ አይችልም።
14እኔ ለኤፍሬም እንደ አንበሳ፣
ለይሁዳም እንደ ደቦል አንበሳ
እሆናለሁና፤
ሰባብሬና አድቅቄአቸው እሄዳለሁ፤
ነጥቄ እወስዳቸዋለሁ፤ ማንም
ሊያድናቸው አይችልም።
15በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ፣
ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ፤
ፊቴን ይሻሉ፤
በመከራቸውም አጥብቀው
ይፈልጉኛል።"

## የእስራኤል ንስሐ አለመግባት

6 "ኑ፤ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤
እርሱ ሰባብሮናል፤

[a]11 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጒም አይታወቅም

5፥4 ኢ4፥22፤ ሆሴ4፥6፡11፤7፥10
5፥5 ኢሳ3፥9፤ 2፥19፤ሕዝ14፥7፤ ሆሴ7፥10፤14፥1
5፥6 ምሳ1፥28፤ኢሳ 1፥15፤ሕዝ8፥6፤ ሚክ6፥67፤ሚል1፥10
5፥7 ኢሳ1፥14፤ 24፥16፤ሆሴ2፥4፡ 11-12፤6፥7
5፥8 ዘኍ10፥2፤ኢሱ 7፥2፤መሳ19፥12፤ኢሳ 10፥29፤ኤር4፥21፤ ሕዝ33፥3፤ሆሴ4፥15፤ 9፥9፤10፥5፡9
5፥9 ኢሳ7፥16፤ 37፥3፤46፥10፤ሆሴ 9፥11-17፤ዘካ1፥6
5፥10 ዘዳ19፥14፤ ሕዝ7፥8
5፥11 ሆሴ9፥16፤ ሚክ6፥16
5፥12 ኢዮ13፥28፤ 18፥16፤ኢሳ51፥8
5፥13 ኢሳ3፥7፤7፥ 16፤ሰቆ5፥6፤ሕዝ23፥ 5፤ሆሴ2፥7፤7፥8፡11፤ 8፥9፤10፥6፤12፥1፤14፥3
5፥14 ዘዳ32፥39፤ ኢዮ10፥16፤ኤር4፥7፤ ሆሴ6፥1፤አሞ3፥4፤ ሚክ5፥8
5፥15 ዘሌ26፥40፤ ዘኍ21፥7፤መዝ24፥6፤ 50፥15፤ኢሳ18፥4፤ 64፥9፤ኤር2፥27፤ሕዝ 20፥43፤ሆሴ3፥5
6፥1 ዘኍ12፥13፤ ዘዳ32፥39፤ኢዩ5፥18፤ 16፥9፤ኢሳ10፥20፤ 19፥22፤ኤር3፥22፤ 30፥17፤ሰቆ3፥11፤

ለከት ነው። *አመንዝረሃል፤* 1፥2፤ 4፥10፡18 ይመ።

5፥4 *የሠሩት ሥራ፤* 4፥9፤ 7፥2፤ 9፥15፤ 12፥2 ይመ። በተደጋጋሚ ኀጢአት መሥራት በንስሓ የመመለስን አዝማሚያ ያጨልማል (ኤር 13፥23፤ ዮሐ 8፥34፤ ሮሜ 6፥6፡16 ይመ)። *የአመንዝራነት መንፈስ፤* 4፥12 ይመ። *እግዚአብሔርንም አያውቁትም* 4፥6፤ ኢሳ 1፥2-4 ይመ።

5፥5 *ትዕቢት፤* ግትር በመሆን በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ዐመፅ ነው (ዘዳ 1፥43፤ 1ሳሙ 15፥23፤ ነህ 9፥16፤ ኢዮ 35፥12፤ መዝ 10፥2፤ ሕዝ 16፥56-57 ይመ)። *ይመሰክራል፤* ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ባቀረበው ክስ አማካይነት ነው (4፥1 እና ማብ ይመ)። *ይሰናከላሉ፤* ጥፋት ያገኛቸዋል (4፥5 ይመ)። *ይሁዳም፤* በመግቢያው ላይ፣ "አሐፊውና የተጻፈበት ጊዜ" የሚለውን ይመ።

5፥6 *እግዚአብሔርን ለመሻት፤* በጸሎትና መሥዋዕት በማቅረብ ወደ እግዚአብሔር መቅረብን ያመለክታል (3፥5፤ አሞ 5፥4-5 ይመ)። *ሊያገኙት አይችሉም፤* ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው መሥዋዕት ማቅረብ ከንቱ ድካም ነበር (2፥7 ይመ፤ ከኢሳ 1፥10-14፤ አሞ 5፥21-25፤ ሚክ 6፥6-8 ጋር ያነጻጽሩ)። እስራኤል እግዚአብሔርን ልታገኘው የምትችለው በፍጹም ልብ ወደ እርሱ ከተመለሰች ብቻ ነው (3፥5፤ 5፥15፤ ዘዳ 4፥29-31፤ ኤር 29፥13 ይመ)።

5፥7 *ታማኞች አልሆኑም፤* ኤር 5፥11 ይመ። *ዲቃሎች፤* ወደ በኣል በመጸለይ የወለዱአቸው ልጆች ናቸው፤ ልጅ በሚወለዱበት ጊዜ በሚደረገውም ሥርዐት በኣልን ያመሰግናሉ። *የወር መባቻ፤* በየጊዜው የሚከበር በዓል ነው (2፥11፤ 1ሳሙ 20፥5፡18፤ አሞ 8፥5፤ ቈላ 2፥16 ይመ)፤ አሁን ግን የፍርድ ጊዜ ነው፤ ወይም የተወሰነባቸውን ቅጣት ለመጨረስ አንድ ወር እንደሚበቃቸው የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

*5፥8፤* የአራም ሰዎችና (ሶርያውያን) በኤፍሬማውያን (እስራኤላውያን) መካከል የተደረገው ጦርነት (2ነገ 16፥5-9፤ ኢሳ 7፥1-9) ለዚህ ንግር ታሪካዊ ዳራ እንደ ሆነ አንዳንድ ተርጓሚዎች ይጠቁማሉ። *እንቢልታ፤* ከአውራ በግ ቀንድ የሚሠራ ሲሆን፣ የጠላትን ጦር መምጣት ለማስታወቅ ይጠቀሙበት ነበር (8፥1 ይመ)። *ጊብዓ፤* ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን ሦስት ኪሎ ሜትር ተኩል ርቆ የሚገኝ ቦታ ነው። *ራማ፤* ከጊብዓ በስተ ሰሜን የሚገኝ ቦታ ነው። *ቤትአዌን፤* የ4፥15 ማብ ይመ። *ብንያም ሆይ፤ መጡብህ!* ብንያማውያን በጦርነት ጊዜ የሚሉት ሽለላ እንደ ሆነ ይገመታል (መሳ 5፥14 ይመ)።

5፥9 *ባድማ፤* ኤር 25፥11፡38 ይመ።

5፥10 *የወሰን ድንጋዮችን እንደሚነቅሉ፤* ይሁዳ የእስራኤልን ግዛት ይዞ ነበር (1ነገ 15፥16-22፤ ዘዳ 19፥14፤ 27፥17፤ ምሳ 22፥28፤ 23፥10፤ ኢሳ 5፥8፤ ሚክ 2፥2 ይመ)። *ቍጣዬ፤* 13፥11 ይመ።

5፥12 *ብል... ነቀዝ፤* ሁለቱም ጥፋት የሚያደርሱ ነፍሳት ናቸው (ኢዮ 13፥28)።

5፥13 *ሕመሙን... ቍስሉን፤* በጠላቶቻቸው እጅ ከደረሰባቸው ሥቃይ የተነሣ ያገኛቸውን የጋራ ቍስል የሚያሳይ ተለዋጭ ዘይቤ ነው (ኢሳ 1፥5-6፤ 17፥4፡11፤ ኤር 30፥12-13 ይመ)። *ወደ አሦር ሄደ፤* ምናሔም እና ሆሴዕ የተባሉ የእስራኤል ነገሥታት፣ ለአሦር ንጉሥ ለሟልሳዊ ቴልጌልቴልፌልሶር ግብር መገበራቸውን የአሦራውያን ጽሑፍ ይገልጻል (2ነገ 15፥19-20፤ 17፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። *ሊፈውስ አይችልም፤* ተባባሪዎቹ መንግሥታት የማይጠቅሙት ነበሩ።

5፥14 *አንበሳ፤* 13፥7 ይመ። እግዚአብሔር ሰውን መሣሪያ አድርጎ በመጠቀም ሊቀጣ ይችላል (ኢሳ 10፥5-6)፤ ነገር ግን በእስራኤል ላይ ስላደረሰው ምሕረት የለሽ ቅጣት፣ ያ ሰው ተጠያቂ ነው (ኢሳ 5፥29፤ 42፥22፤ አሞ 9፥14፤ ሚክ 5፥8 ይመ)።

5፥15 *ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ፤* እስራኤል ተስፋ ከመቁረጧ የተነሣ እውነተኛ ንስሓ እስክምትገባ ድረስ፣ እግዚአብሔር ከእርሷ ፊቱን እንደሚመልስ በማስፈራራት ተናግሮአል፤ ይህም፣ ከዚህ ቀጥሎ ለሚቀርበው የነቢዩ መሪ ሐሳብ የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል።

6፥1 *እንመለስ፤* ከልብ ያልሆነ (ቍ 4 ይመ) የንስሓ ሐሳብ ነው፤ በ5፥13-15 ላይ እንደተጠቀሰው እውነተኛ አዳኝ አሦር ሳይሆን (ከ5፥13 ጋር ያነጻጽሩ) እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን እስራ

እርሱም ይጠግነናል፤
እርሱ አቍስሎናል፤
እርሱም ይፈውሰናል።
2ከሁለት ቀን በኋላ ያነቃናል፤
በእርሱም ፊት እንድንኖር፣
በሦስተኛው ቀን ያስነሣናል።
3እግዚአብሔርን እንወቀው፤
የበለጠ እናውቀውም ዘንድ እንትጋ፤
እንደ ንጋት ብርሃን፣
በእርግጥ ይገለጣል፤
ምድርን እንደሚያረሰርስ የበልግ ዝናብ፣
እንደ ክረምትም ዝናብ ወደ እኛ
ይመጣል።"

4"ኤፍሬም ሆይ፤ ምን ላድርግህ?
ይሁዳ ሆይ፤ ምን ላድርግህ?
ፍቅራችሁ እንደ ማለዳ ጉም፣
እንደሚጠፋም የጧት ጤዛ ነው።
5ስለዚህ በነቢያቴ ቈራረጥኋችሁ፤
በአፌም ቃል ገደልኋችሁ፣
ፍርዴም እንደ መብረቅ በላያችሁ አበራ።
6ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፣
ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ
እግዚአብሔርን ማወቅ እሻለሁና።
7እንደ አዳም[ሀ] ቃል ኪዳንን ተላለፉ፤
በዚያም ለእኔ ታማኝ አልነበሩም።
8ገለዓድ በደም የተበከለች፣
የክፉዎች ሰዎች ከተማ ናት።
9ወንበዴዎች ሰውን ለማጥቃት
እንደሚያደቡ፣
ካህናትም በቡድን እንዲሁ ያደርጋሉ፤
በሴኬም መንገድ ላይ ሰዎችን ይገድላሉ፤
አሳፋሪም ወንጀል ይፈጽማሉ።
10በእስራኤል ቤት
የሚሰቀጥጥ ነገር አይቻለሁ፤
በዚያ ኤፍሬም ዘማዊ ሆነ፤
እስራኤልም ረከሰ።

11"ይሁዳ ሆይ፤ ለአንተም፣
መከር ተመድቦብሃል።
ሕዝቤን ከምርኮ አገር በመለስሁ ጊዜ፣
7 እስራኤልን በምፈውስበት ጊዜ፣
የኤፍሬም ኀጢአት፣
የሰማርያም ክፋት ይገለጣል።
እነርሱ ያጭበረብራሉ፤
ሌቦች ቤቶችን ሰብረው ይገባሉ፤
ወንበዴዎችም በየመንገድ ይዘርፋሉ።
2ነገር ግን ክፉ ድርጊታቸውን ሁሉ
እንደማስታውስ፣
እነርሱ አይገነዘቡም፤
ኀጢአታቸው ከቦአቸዋል፤
ሁልጊዜም በፊቴ ናቸው።

3"ንጉሡን በክፋታቸው፣
አለቆችንም በሐሰታቸው ያስደስታሉ።
4ሊጡ በክቶ ኩፍ እንደሚል፣
ዳቦ ጋጋሪው እሳት መቈስቈስ
እስከማያስፈልገው ድረስ፣
እንደሚነድ ምድጃ፣
ሁሉም አመንዝራ ናቸው።

[ሀ]7 ወይም በአዳም እንደ ሆነው ወይም በሰዎች

ሆሴ5፥14፤14፥4
6፥2 መዝ30፥5፤ 71፥20፤80፥18፤ ማቴ16፥21
6፥3 ኢዩ4፥3፤መዝ 72፥6፤ሆሴ11፥10፤ 12፥6
6፥4 ሆሴ7፥1፤ 11፥8፤13፥3
6፥5 ኤር1፥9፣10፤5፥14፤23፥29፤ዕብ4፥12
6፥6 1ሳሙ15፥22፤ መዝ40፥6፤ኢሳ1፥11፤ ኤር4፥22፤ሆሴ2፥20፤ ሚክ6፥8፤ማቴ9፥13፤ 12፥7፤ማር12፥33
6፥7 ዘፍ9፥11፤ኤር 11፥10፤ሆሴ5፥7፤8፥7
6፥8 ሆሴ12፥11
6፥9 መዝ10፥8፤ኤር 5፥30፣31፤7፥9-10፤ ሕዝ22፥9፤ሆሴ4፥2፤ 5፥1፤7፥1
6፥10 ኤር5፥30፤ 23፥14፤ሕዝ23፥7፤ ሆሴ5፥3
6፥11 ኤር51፥33፤ ኢዩ3፥13
7፥1 ቍ13፤ዘፀ22፥ 2፤መዝ126፥1፤ሕዝ 24፥13፤ሆሴ4፥2፤6፥4፡ 9፤12፥1፤ሶፎ2፥7
7፥2 ኢዮ35፥15፤ኤ ር2፥19፤4፥18፤14፥10 ፤44፥21፤ሆሴ8፥13፤9 ፥15
7፥3 ኤር28፥14፤ ሆሴ4፥2፤10፥13፤ ሚክ7፥3
7፥4 ኤር9፥2

ኤል ዐውቃለች (ከ7፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

6፥2 *ከሁለት ቀን... በሦስተኛው ቀን፤* ለአጭር ጊዜ እንደ ሆነ ያመለክታል። እስራኤል የእግዚአብሔር ቍጣ ለጊዜው ብቻ መሆኑን ገምታ ነበር።

6፥3 *እግዚአብሔርን እንወቀው፤* የሆሴዕ መጽሐፍ ጽንሰ ሐሳብ ነው (ቍ6፤ 2፥8፡20፤ 4፥1፡6፤ 5፥4 ይመ)። *የበልግ ዝናብ፣ እንደ ክረምትም ዝናብ፤* ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ በመዝነብ ምድርን እንደሚያድሳት ሁሉ፣ እስራኤልም የእግዚአብሔር ምሕረት ወደ እርሷ ተመልሶ እንደሚያድሳት ታምን ነበር።

6፥4 *ኤፍሬም፣* የሰሜኑን መንግሥት እስራኤልን ያመለክታል። *ምን ላድርግህ?* ኢሳ 5፥4 ይመ። እግዚአብሔር የእስራኤልን የማስመሰል ንስሓ ተመልክቶአል። *ይሁዳ፤* በመዝሙሩ ላይ፣ "ጸሓፊና የተጻፈበት ጊዜ" የሚለውን ይመ። *ፍቅራችሁ፤* 2፥19 እና የቍ 6 ማብ ይመ *እንደ ማለዳ ጉም... የጧት ጤዛ፤* ጊዜያዊ የሆነን ነገር የሚያሳይ ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው።

6፥5 *ነቢያቴ፤* የእግዚአብሔር አፍ በመሆን የሕዝቡን ኀጢአት አውግዘዋል (ኤር 1፥9፤ 15፥19 ይመ)። *በአፌም ቃል፤* በእግዚአብሔር ታማኝ ነቢያት የተነገሩ ፍርዶች ናቸው። *እንደ መብረቅ፤* ዘዳ 32፥41 ይመ።

6፥6 *ምሕረትን፤* በዕብራይስጥ "ሄሴድ" የሚለው ቃል ሰው ለባልንጀራው የሚያሳየውን ቀና ባሕርይ ወይም ለእግዚአብሔር ያለውን ሉሌነት እንዲሁም እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ የሚጠብቀውን ሁሉ በጥቅሉ የሚያመለክት ሲሆን፣ በዚህ ክፍል ሁለቱንም ሳያመለክት አይቀርም። በቍ 4 ይኸው የዕብራይስጥ ቃል፣ "ፍቅር" ተብሎ ተተርጕሞአል። *መሥዋዕት ይልቅ፤* ለእግዚአብሔር ፈቃድ ታማኝ ሳይሆኑ መሥዋዕት ማቅረብ በእርሱ ዘንድ ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም (1ሳሙ 15፥22-23፤ ኢሳ 1፥11-20፤ ኤር 7፥21-22፤ አሞ 5፥21-24፤ ሚክ 6፥6-8፤ ማቴ 9፥13፤ 12፥7 ይመ)።

6፥7 *እንደ አዳም፤* መጽሐፍ ቅዱስ ከአዳም ጋር ኪዳን መደረጉን ስላልገለጸ ኢርቱዓዊው ማስረጃ እርግጠኛነት የለውም። በዐረፍተ ነገሩ መካከል ላይ፣ "በዚያም" ለሚለው ቃል የገባው አማራጭ ትርጕም እንደሚጠቍመው በዮርዳኖስ (ኢያ 3:16) አካባቢ "አዳም" የሚባል ስፍራ መኖሩን ያሳያል። አዳም ለሚለው ቃል የተሰጠ ሦስተኛ ትርጕም፣ የሰው ዘር የሚል ነው (አማራጭ ትርጕሙን ይመ)። *ቃል ኪዳን ተላለፉ፤* 8፥1፤ ኢያ 7፥11 ይመ።

6፥8 *ገለዓድ፤* 12፥11፤ መሳ 10፥17፤ 12፥7 ይመ። *በደም የተበከለች፤* ይህ ኢርቱዓዊ ሐረግ ግልጽ አይደለም፤ ነገር ግን በመሳ 12፥1-6 ላይ ከተጠቀሰው የደም መፍሰስ ይልቅ፣ ሆሴዕ በቅርብ ስለ ሆነው ነገር መናገሩ ይሆናል (2ነገ 15፥25 ይመ)።

6፥9 *ይገድላሉ፤* ይህ ድርጊት የተፈጸመበት ወቅት አይታወቅም።

6፥10 *ዘማዊ፤* ም 2 እና 4ን ይመ።

6፥11 *መከር፤* የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው (8፥7፤ 10፥12-13፤ ኤር 51፥33፤ ኢዩ 3፥13፤ ማቴ 13፥39፤ ራእ 14፥15 ይመ)። *ሕዝቤን... በመለስሁ ጊዜ፤* "በምፈውስበት" ከሚለው ቃል ጋር ተጓዳኝ ሲሆን፣ ሐረጉ የቈሰለውን መላው የእስራኤልን ሕዝብ መታደስ የሚያመለክት ነው (ኢዩ 3፥1፤ ሶፎ 3፥20 ይመ)።

7፥1 *በምፈውስበት፤* 5፥13፤ 6፥1፤ 11፥3፤ 14፥4፤ ኤር 51፥8-9 ይመ። *የኤፍሬም፤* የሰሜኑን መንግሥት እስራኤልን ያመለክታል። *ኀጢአት፤* 4፥8፤ 5፥5፤ 8፥13 ይመ። *የሰማርያም፤* የሰሜኑ መንግሥት ሌላው ስም ሲሆን፣ ዘንበሪ የእስራኤል ዋና ከተማ እንድትሆን ስለ መረጣት 1ነገ 16፥24 የንጉሡ መቀመጫ ከተማ ሆነች። *ክፋት፤* ቍ3 ይመ። *ይገለጣል፤* እግዚአብሔር ያየዋል። *ያጭበረብራሉ፤* ኤር 6፥13፤ 8፥10 ይመ፤ በማስመሰል የገቡትን ንስሓና በተንኰል ከሌሎች ጋር የፈጠሩትን ኅብረት ያመለክት ይሆናል። *ሌቦች፤* 4፥2 ይመ። *ወንበዴዎችም፤* 6፥9፤ ዘፍ 49፥19፤ ኤር 18፥22 ይመ።

7፥2 *እንደማስታውስ፤* ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ፊት የተራቈተ ነው (መዝ 90፥8 ይመ)፤ ክፉዎች ግን እግዚአብሔር የማያይ ይመስላቸዋል (መዝ 10፥6፡11፤ 14፥1፤ ሕዝ 8፥12 ይመ)።

7፥3 *ንጉሡን... ያስደስታሉ፤* በቤተ መንግሥት ከተደረጉት ዐመፆች በአንዱ ውስጥ መሳተፋቸውን ሊያመለክት ይችላል (2ነገ 15፥8-30 ይመ)። *ንጉሡን... አለቆችንም፤* በ3፥4፤ 8፥4፤ 13፥10 ላይም ተጣምረዋል። *በሐሰታቸው፤* 11፥12፤ መዝ 59፥12፤ ናሆ 3፥1 ይመ።

7፥4 *ዳቦ ጋጋሪው፤* ሤራውን የሚመራውን ሰው ሊያመለክት ይችላል። *እሳት፤* የፖለቲካ ሤራን የሚያመለክት ተለዋዋጭ ዘይቤ ነው (ቍ6-7 ይመ)። እሳት፤ በአገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት ተዳፍኖ ይቀመጣል፤ ባስፈለገም ጊዜ እንዲነድ ይደረጋል። *አመንዝራ፤* 3፥1፤ 4፥2፡13፤ ኤር 9፥2፤ ሕዝ 23፥37 ይመ።

5በንጉሣችን የበዓል ቀን፣
አለቆች በወይን ጠጅ ስካር ጋሉ፤
እርሱም ከፌዘኞች ጋር ተባበረ።
6ልባቸው እንደ ምድጃ የጋለ ነው፤
በተንኰል ይቀርቡታል፤
ቍጣቸው ሌሊቱን ሙሉ ይጤሳል፤
እንደሚነድም እሳት በማለዳ
ይንበለበላል።
7ሁሉም እንደ ምድጃ የጋሉ ናቸው፤
ገዦቻቸውን ፈጁ፤
ንጉሦቻቸው ሁሉ ወደቁ፤
ከእነርሱም ወደ እኔ የቀረበ ማንም
የለም።

8"ኤፍሬም ከአሕዛብ ጋር ተደባለቀ፤
ኤፍሬም ያልተገላበጠ ቂጣ ነው።
9እንግዶች ጕልበቱን በዘበዙ፤
እርሱ ግን አላስተዋለም።
ጠጕሩም ሽበት አወጣ፤
እርሱ ግን ልብ አላለም።
10የእስራኤል ትዕቢት በራሱ ላይ
መሰከረበት፤
ይህ ሁሉ ሆኖ ግን፣
ወደ ስምላኩ ወደ *እግዚአብሔር*
አልተመለሰም፤
እርሱንም አልፈለገም።
11ኤፍሬም በቀላሉ እንደምትታለል፣
አእምሮም እንደሌላት ርግብ ነው፤
አንድ ጊዜ ወደ ግብፅ ይጣራል፤
ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ አሦር ይዞራል።
12ሲበሩ፣ መረቤን በላያቸው እዘረጋለሁ፤
እንደ ሰማይ ወፎችም ጐትቼ
አወርዳቸዋለሁ፤
ስለ ክፉ ሥራቸውም በጉባኤ መካከል
እቀጣቸዋለሁ።
13ወዮ ለእነርሱ፤
ከእኔ ርቀው ሄደዋልና!
ጥፋት ይምጣባቸው!
በእኔ ላይ ዐምፀዋልና።
ልታደጋቸው ፈለግሁ፤
እነርሱ ግን በእኔ ላይ ሐሰት ይናገራሉ።
14ከልባቸው ወደ እኔ አይጮኹም፤
ነገር ግን በዐልጋቸው ላይ ሆነው
ያለቅሳሉ።
ስለ እህልና ስለ አዲስ የወይን ጠጅ
ይሰበሰባሉ፤
ነገር ግን ከእኔ ዘወር ብለዋል።
15እኔ አሠለጠንኋቸው፤ አጠነከርኋቸውም፤
እነርሱ ግን አደሙብኝ።
16ወደ ከንቱ ነገር ተመለሱ፤
ዒላማውን እንደ ሳተ ቀስት ናቸው፤
መሪዎቻቸው ስለ ክፉ ቃላቸው፣
በሰይፍ ይወድቃሉ፤
በዚህም ምክንያት በግብፅ ምድር፣
መዘባበቻ ይሆናሉ።

## እስራኤል ዐውሎ ነፋስን ታጭዳለች

8 "መለከትን በአፍህ ላይ አድርግ፤
ሕዝቡ ቃል ኪዳኔን አፍርሰዋልና፣
በሕጌም ላይ ዐምፀዋልና፣
ንስር *በእግዚአብሔር* ቤት ላይ ነው፤
2እስራኤልም፣ 'አምላካችን ሆይ፤ እኛ
እናውቅሃለን' እያሉ፣
ወደ እኔ ይጮኻሉ።
3ነገር ግን እስራኤል በጎ የሆነውን ነገር
ናቀ፤

7፥5 መዝ1፥1፤ኢሳ 28፥1፡7
7፥6 መዝ21፥9
7፥7 ቍ16፤መዝ 14፥4፤ኢሳ9፥13፤ሆሴ 13፥10፤ሶፎ1፥6
7፥8 ቍ11፤መዝ 106፥35፤ሆሴ5፥13
7፥9 ኢሳ1፥7፤ ሆሴ8፥7
7፥10 ቍ14፤ኢሳ 9፥13፤ሆሴ5፥4፡5
7፥11 ቍ8፡16፤ዘፍ 8፥8፤ኤር2፥18፤ሰቆ5፥ 6፤ሆሴ9፥3፡6፤12፥1
7፥12 ሕዝ12፥13፤ 32፥3
7፥13 ቍ1፤መዝ 116፥11፤ኤር14፥10፤ 51፥9፤ሕዝ34፥46፤ ሆሴ9፥12፡17፤ ማቴ23፥37
7፥14 ቍ10፤ኤር 3፥10፤ሆሴ4፥10፤9፥1 ፤13፥16፤አሞ2፥8
7፥15 መዝ2፥1፤ 140፥2፤ሆሴ11፥3፤ ናሆ1፥9፡11
7፥16 ቍ7፡11፤መዝ 78፥9፡57፤ሕ ዝ23፥32፤ ሆሴ9፥3፤11፥5፤ሚል 3፥14
8፥1 ዘኍ10፥2፤ ዘዳ28፥49፤ኤር4፥13፤ 11፥10፤ሆሴ4፥6፤6፥7
8፥3 ማቴ7፥23፤ ቲቶ1፥16

7፥5 *በንጉሣችን የበዓል ቀን፤* መጠጥ የተራጨበት የንግሥ ወይም የልደት በዓል ግብዣ ሊሆን ይችላል። ንጉሥ ኤላ የተገደለው በስካር ሳለ ነው (1ነገ 16፥9-10)። *ከፌዘኞች፤* ምሳ 21፥24 ይመ። ኢሳይያስ የእስራኤልን ሰካራምነትና ፌዘኞቿን አወገዘ (28፥1-8፡14)።

*7፥6፤* ምቹ ጊዜ እስከሚመጣ ድረስ ሤራው በምስጢር ይጠበቅ ነበር።

7፥7 *ገዦቻቸውን... ንጉሦቻቸው፤* በሃያ ዓመት ጊዜ ውስጥ አራት ንጉሦች ተገደሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ ዘካርያና ሰሎም የተገደሉት በሰባት ወር ጊዜ ውስጥ ነው (2ነገ 15፥10-15)። *ከእነርሱም ወደ እኔ የቀረበ ማንም የለም፤* ለመዋረዳቸው ዋናው መንሥኤ ይህ ነበር።

7፥8 *ያልተገላበጠ ቂጣ፤* ትክክለኛ ያልሆነ መመሪያን የሚገልጽ ተለዋጭ ዘይቤ ነው፤ በጋለ ምድጃ የተጋገረና (ከ1ነገ 19፥6 ጋር ያነጻጽሩ) ሥሩ ያረረ ላዩ ደግሞ ያልበሰለ ነው።

7፥9 *ጠጕሩም ሽበት፤* ያለ ጊዜው አረጀ፤ ይህ የአደጋ ምልክትም አላሳሰበውም። ለቴልጌልቴልፌልሶር (2ነገ 15፥19-20፡29) እና ለግብፅ የሚከፈለው ግብር የአገሪቱን ምጣኔ ሀብት አዳከመው።

7፥10 *አልተመለሰም፤* 3፥5፤ 5፥4፤ አሞ 4፥6-11 ይመ። *አልፈለገም፤* 2፥7፤ 5፥6 ይመ።

7፥11 *አእምሮም እንደሌላት፤* ኤር 5፥21 ይመ። ምናሔ ወደ አሦር (2ነገ 15፥19-20)፣ ፋቁሔም ወደ ግብፅ ፊታቸውን መለሱ፤ ንጉሡ ሆሼዕ ግን በማለዋወጥ ከሁለቱም ጋር ኅብረት ፈጠረ (2ነገ 17፥4)። *ርግብ፤* ለየት ያለ ዘይቤ የያዘውን 11፥11 እና ማብ እንዲሁም የመዝ 68፥13 ማብ ይመ።

7፥12 *መረቤን፤* የሚያጠምደው ራሱ እግዚአብሔር እንጂ ሕዝቦች አይደሉም፤ እስራኤልም ተጠምዶ እንደሚያዝ ርግጠኛ ነበር።

7፥13 *ወዮ፤* ብዙ ጊዜ ከፍርዱ ጋር ተያይዞ ይጠቀሳል (9፥12 ይመ)። *ጥፋት፤* 9፥6፤ ኢሳ 13፥6 ይመ። *ልታደጋቸው፤* 13፥14 ይመ፤ ከግብፅ ነጻ ስለ መውጣት በሚናገረውም ክፍል ይህ ቃል ተጠቅሶአል (ዘፀ 6፥6፤ ሚክ 6፥4 ይመ)። *ሐሰት፤* ቢል ጽግና እንዲሁም የወደፊት የሰው ዕጣ ፈንታ በእግዚአብሔር ሳይሆን በአማልክት እጅ መሆኑን ማሰባቸው ሊሆን ይችላል።

7፥14 *ያለቅሳሉ፤* ኢል 1፥13 ይመ። *ስለ እህልና ስለ አዲስ የወይን ጠጅ፤* 2፥8፡22፤ 9፥1-2 ይመ። *ይሰበሰባሉ፤* ከዘሌ 19፥28፤ 21፥5 ጋር ያነጻጽሩ።

7፥15 *አሠለጠንኋቸው፤* ልጆች ወይም ወታደሮች እንደሚሠለጥኑ ማለት ነው። *አጠነከርኋቸው፤* ቃል በቃል ሲተረጐም ክንዳቸውን አበረታለሁ ማለት ነው (ሕዝ 30፥24-25 ይመ)።

7፥16 *ዒላማውን እንደ ሳተ ቀስት፤* መዝ 78፥57 ይመ። ቀስት ዒላማውን እንደ ሚስት ሁሉ፣ እስራኤልም ማንነቷን ሳተች። *በግብፅ፤* 8፥13፤ 9፥6፤ 11፥5 ይመ። ቍጥሩ ብዙ የሆነ ሕዝብ ወደ ግብፅ ተገዶ ስለ መሰደዱ የተጻፈ ነገር የለም፤ ነገር ግን ጥቂት ምርኮኞች ወደዚያ ተወስደዋል (2ነገ 23፥34፤ ኤር 22፥11-14)፤ እንዲሁም ጥቂት ስደተኞች በፈቃዳቸው ወደዚያ ሄደዋል (2ነገ 25፥26፤ ኤር 42-44)። በ11፥11፤ ኢሳ 11፥11፤ 27፥13፤ ዘካ 10፥10 ላይ ከግብፅ መመለሳቸው አስቀድሞ ተነግሮአል። *መዘባበቻ፤* ግብፅ እስራኤልን አትረዳም፤ የእግዚአብሔርንም ኀይል ታቃልላለች (ዘዳ 9፥28 ይመ)።

8፥1 *መለከትን፤* የማስጠንቀቂያ ምልክት ለመስጠት የሚነፋ መሣሪያ ነው (5፥8፤ ኢል 2፥1፤ አሞ 3፥6 ይመ)። *ቃል ኪዳኔን፤* ቃል ኪዳኑ የሚጠይቀው ነገር ለማለት ነው። *ንስር፤* አሦርን ያመለክታል። *በእግዚአብሔር ቤት፤* ቤተ መቅደሱን ብቻ ሳይሆን፣ የእስራኤልንም ምድር ያመለክታል (9፥15 እና ማብ ይመ፤ ከዘዳ 15፥17 ጋር ያነጻጽሩ)።

8፥2 *እናውቅሃለን፤* ቍ 3-6 እንደሚያመለክተው፣ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት አምልኮ፣ ሌሎች አማልክትን ለማምለክ ከነበራቸው ሐሳብና ልምምድ የተነሣ እጅግ ተበላሽቶአል (አሞ 2፥4፡7-8፤ 3፥14፤ 5፥26 ይመ)።

ጠላትም ያሳድዳቸዋል።
4 ያለ እኔ ፈቃድ ነገሥታትን አነገሡ፤
እኔንም ሳይጠይቁ አለቆችን መረጡ፤
በብራቸውና በወርቃቸው፣
ለገዛ ጥፋታቸው፣
ጣዖታትን ለራሳቸው ሠሩ።
5 ሰማርያ ሆይ፤ የጥጃ ጣዖትሽን ጣይ፤
ቍጣዬ በእነርሱ ላይ ነድዶአል፤
የማይነጹት እስከ መቼ ነው?
6 ይህም በእስራኤል ሆነ!
ባለ እጅ የሠራው ይህ ጥጃ፣ አምላክ
አይደለም፤
ያ የሰማርያ ጥጃ፣
ተሰባብሮ ይደቃል።

7 "ነፋስን ይዘራሉ፤
ዐውሎ ነፋስንም ያጭዳሉ፤
አገዳው ዛላ የለውም፤
ዱቄትም አይገኝበትም፤
እህል አፍርቶ ቢገኝም፣
ባዕዳን ይበሉታል።
8 እስራኤል ተውጠዋል፤
በአሕዛብም መካከል፣
ዋጋ እንደሌለው ዕቃ ሆነዋል።
9 ለብቻው እንደሚባዝን የዱር አህያ፣
ወደ አሦር ሄደዋልና፤
ኤፍሬም በእጅ መንሻ ወዳጅ አበጀ።
10 በአሕዛብ መካከል ራሳቸውን ቢሸጡም፣
እኔ አሁን እሰበስባቸዋለሁ፤
በኀያል ንጉሥ ጭቈና ሥር፣
እየመነመኑ ይሄዳሉ።

11 "ኤፍሬም ለኀጢአት ማስተስረያ ብዙ
መሠዊያዎችን ቢሠራም፣
እነርሱ የኀጢአት መሥሪያ
መሠዊያዎች ሆነውበታል።
12 በሕጌ ውስጥ ያለውን ብዙውን ነገር
ጻፍሁላቸው፤
እነርሱ ግን እንደ እንግዳ ነገር ቈጠሩት።
13 ለእኔ የሚገባውን መሥዋዕት ያቀርባሉ፤
ሥጋውንም ይበላሉ፤
*እግዚአብሔር* ግን በእነርሱ አልተደሰተም፤
ስለዚህ ክፋታቸውን ያስታውሳል፤
ኀጢአታቸውን ይቀጣል፤
ወደ ግብፅም ይመለሳሉ።
14 እስራኤል ፈጣሪውን ረሳ፤
ቤተ መንግሥቶችንም ሠራ፤
ይሁዳም የተመሸጉ ከተሞችን አበዛ፤
እኔ ግን በከተሞቻቸው ላይ እሳትን
እለቅቃለሁ፤
ምሽጎቻቸውንም ይበላል።"

## በእስራኤል ላይ የሚደርሰው ቅጣት

9 እስራኤል ሆይ፤ ደስ አይበልሽ፤
እንደ ሌሎችም ሕዝቦች ሐሤት
አታድርጊ፤
ስስምላክሽ ታማኝ አልሆንሽምና፤
በየእህል ዐውድማውም ላይ፣
ለጋለሞታ የሚከፈለውን ዋጋ ወደሻል።
2 የእህል አውድማዎችና የወይን
መጭመቂያዎች ሕዝቡን አይመግቡም፤
አዲሱም የወይን ጠጅ ይጉድልባቸዋል።
3 *በእግዚአብሔር* ምድር አይቀመጡም፤
ኤፍሬም ወደ ግብፅ ይመለሳል፤
የረከሰውንም ምግብ[ሸ] በአሦር ይበላል።

[ሸ]3 በሥርዐቱ መሠረት ያልነጻ ማለት ነው

8፥4 ሆሴ2፥8፤ 13፥12፡10
8፥5 ቍ6፤ሆሴ 10፥5፤ኤር13፥27
8፥6 ቍ5፤ዘፀ32፥4፤ ኤር16፥20፤ሆሴ14፥3
8፥7 ዘዳ28፥38፤ኢዮ 4፥8፤ምሳ22፥8፤ኢሳ 17፥11፤66፥15፤ሆሴ2 ፥9፤7፥9፤9፥16፤10፥1 2፤13፤ናሆ1፥3፤ገላ6፥8
8፥8 ኤር22፥28፤ 51፥34
8፥9 ዘፍ16፥12፤ ኤር2፥18፤22፥20፤ ሕዝ23፥5፤ሆሴ5፥13
8፥10 ኤር42፥2፤ ሕዝ16፥37፤22፥20
8፥11 ሆሴ10፥1፤ 12፥11
8፥12 ቍ1
8፥13 ኤር6፥20፤7፥ 21፤ሆሴ4፥9፤9፥3፡4፡6 ፡9፤አሞ8፥7
8፥14 ዘዳ32፥18፤ መዝ95፥6፤ኢሳ17፥ 10፤ኤር5፥17፤17፥27 ፤ሆሴ2፥13
9፥1 ዘፍ30፥15፤ መዝ73፥27፤ኢሳ22፥ 12፤13፤24፥16፤ሆሴ7፥ 14፤10፥5
9፥2 ኢሳ24፥7፤ሆሴ 2፥9፤ኢል1፥10
9፥3 ዘሌ25፥23፤ሕዝ 4፥13፤ሆሴ7፥11፡16፤ 8፥13፤10፥5፤አሞ7፥17

8፥4 *ነገሥታትን አነገሡ፤* ከዳግማዊ ኢዮርብዓም በኋላ በዐሥራ ሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አምስት ነገሥታት በእስራኤል ላይ ነግሠዋል (2ነገ 15፥8-30)። ከእነዚህም ሦስቱ የነገሡት ኀይልን በመጠቀም ነበር (7፥7 ይመ)።

8፥5 *የጥጃ ጣዖትሽን፤* ቀዳማዊ ኢዮርብዓም (930-909 ዓ.ቅ.ክ.) በቤተ ልሔምና በዳን የወርቅ ጥጆች በማቆም ለሕዝቡ "አማልክትህ እነዚህ ናቸው" ብሎ ነበር (1ነገ 12፥28-33፤ እና የ1ነገ 12፥28 ማብ ይመ)።

8፥6 *ባለ እጅ የሠራው፤* ጣዖት ማምለክን አስመልክቶ የተነገረውን ትንቢታዊ ምፀት ለማስተዋል ኢሳ 40፥20፤ 41፥22-24፤ 44፥9-20 እንዲሁም መዝ 115፥4-8 ይመ። አሮን (ዘፀ 32፥8) እና ቀዳማዊ ኢዮርብዓም፣ "እነዚህ አማልክትህ ናቸው" አሉ፤ ሆሴዕ ግን ይህ፣ "አምላክ አይደለም" አለ።

8፥7 *ይዘራሉ... ያጭዳሉ፤* የክፉ ሥራን ውጤት የሚገልጽ የተለመደ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው (10፥13፤ ኢዮ 4፥8፤ መዝ 126፤ 5-6፤ ምሳ 11፥18፤ 22፥8፤ 2ቆሮ 9፥6፤ ገላ 6፥7 ይመ)። እስራኤል የጣዖት አምልኮን ነፋስ ዘራች፤ ከአሦር የመጣውንም ዐውሎ ነፋስ አጨደች። *አገዳው... ዱቄትም፤* ነቢዩ፣ ከዕብራይስጥ ቃላት ድምፀት ጋር ተመሳሳይ ድምፀት ባላቸው ቃላት ተጠቅሞአል። *ባዕዳን፤* አሦርን ለማለት ነው።

*8፥8፤* እስራኤል የእግዚአብሔር ሕዝብ ትሆን ዘንድ ተመርጣ ነበር (ዘፀ 19፥5፤ አሞ 3፥2)፤ ነገር ግን ከሌሎች አሕዛብ ጋር ስለ ተደባለቀች ከሌሎች የምትለይበትን ማንነቷን አጣች፤ በእግዚአብሔርም ፊት ተናቀች።

8፥9 *ኤፍሬም በእጅ መንሻ ወዳጅ አበጀ፤* የእሥራኤል ነገሥታት የነበሩት ምናሔም (2ነገ 15፥19) እና ሆሴዕ (2ነገ 17፥3) ለአሦር ንጉሥ ግብር ይከፍሉ ነበር።

*8፥10፤* ምንም እንኳን እስራኤል ለአሦር ንጉሥ ግብር ብትከፍልም፣ ከሥጋት ለመዳን አስተማማኝ ሁኔታን ሊፈጥርላት አልቻለም፤ እንዲያውም እግዚአብሔር እስራኤልን የቀጣው በአሦር አማካይነት ነው፤ በመሠረቱ የእስራኤል ጠላት እግዚአብሔር ራሱ ነበር (2፥8-9፡13፤ 7፥12 ይመ)።

8፥11 *ብዙ መሠዊያዎችን ቢሠራም፤* ለበኣል የተሠሩ መሠዊያዎችን ያመለክታል።

8፥13 *መሥዋዕት ያቀርባሉ፤* ቍ 2 እና ማብ ይመ። *ሥጋውንም ይበላሉ፤* ለመሥዋዕት የሚቀርበው ሥጋ በከፊል በመሥዋዕት አቅራቢውና በቤተሰቡ ይበላ ነበር (ዘሌ 7፥11-18፤ ዘዳ 12፥7፤ ኤር 7፥21 ይመ)። *በእነርሱ አልተደሰተም፤* የ6፥6 ማብ ይመ። *ግብፅም፤* በአሦርና በግብፅ ላይ የታመነችው እስራኤል፤ ተመልሳ ወደ ግብፅ መሄድ ነበረባት፤ ይኸውም በባዕድ ምድር በባርነት ለመኖር ሲሆን፣ በመጀመሪያ ለአሦር ተገዛች (9፥3 ይመ)፤ ነገር ግን የ7፥16 ማብ ይመ።

8፥14 *እስራኤል... ረሳ፤* የችግራቸው ሁሉ ምክንያት ይህ ነው (ከመሳ 2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። *ቤተ መንግሥቶችንም ሠራ... የተመሸጉ ከተሞችን አበዛ፤* እስራኤል የተመካችው በፈጣሪዋ ሳይሆን፣ በራሷ የእጅ ሥራ ነበር። *ይሁዳም፤* በዚህ መጽሐፍ በመግቢያ ላይ "ጸሐፊና የተጻፈበት ዘመን" የሚለውን ይመ። *እሳትን፤* አሞ 1፥4፡7፡10፡14፤ 2፥5 ይመ።

*9፥1፤* ይህ ጥቅስ እንደ ዳስ በዓል ባሉ የመከር በዓላት ላይ የሚነሣውን ሐሳብ በመናገር ይጀምራል (ዘሌ 23፥33-43፤ ዘዳ 16፥13-15)። *ታማኝ አልሆንሽምና፤* 1፥2፤ 2፥2-5 ይመ። *ለጋለሞታ የሚከፈለውን፤* 2፥5፡12 ይመ። ትርጕሙ ቃል በቃል ሳይሆን ከመንፈሳዊ ገጽታውና አንጻር መታየት አለበት። *በየእህል ዐውድማው ላይ፤* እህል በሚወቃበት ወራት፣ የገበሬው ልብ ወደ ዐውድማው ነው፤ እህል የሚወቁ ሰዎችም እህሉን ለመጠበቅና በመጨረሻም የደስታው ግብዣ ተካፋዮች ለመሆን ሌሊቱን ሁሉ በዚያው ያሳልፋሉ፤ ዝሙት አዳሪዎችም በስፍራው መገኘት የተለመደ ነበር (ሩት 3፥2-3 እና ማብ ይመ)።

9፥3 *በእግዚአብሔር ምድር፤* እግዚአብሔር የራሴ ናት የሚላትን የተስፋዪቱን ምድር ያመለክታል (ከዘሌ 25፥23፤ ኢሱ 22፥19፤ ኤር 2፥7፤ ሕዝ 38፥16፤ ኢል 1፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። *ኤፍሬም፤* የሰሜኑን መንግሥት እስራኤልን ማለት ነው። *ግብፅ... በአሦር፤* እስራኤል ተስፋ ወዳረገቻቸውና የቤተ መቅደሱን መሥዋዕት ማቅረብ ወደማትችልበት ምድር (8፥13 እና ማብ ይመ) ልትሰደድ ተገደደች። *የረከሰውንም፤* የባዕድ አገር እንደ

4የወይን ጠጅን ቍርባን *ለእግዚአብሔር*
አያፈስሱም፤
*መሥዋዕታቸውም* ደስ አያሰኘውም፤
እንዲህ ዐይነቱ *መሥዋዕት* ለእነርሱ
የሐዘንተኞች እንጀራ ይሆንባቸዋል፤
የሚበሉትም ሁሉ ይረክሳሉ።
ይህ ምግብ ለገዛ ራሳቸው ይሆናል፤
ወደ *እግዚአብሔርም* ቤተ *መቅደስ*
አይገባም።
5*በእግዚአብሔር* የበዓል ቀናት፣
በዓመት በዓሎቻችሁም ቀን ምን
ታደርጋላችሁ?
6ከጥፋት ቢያመልጡም እንኳ፣
ግብፅ ትሰበስባቸዋለች፤
ሜምፎስም ትቀብራቸዋለች።
የብር ሀብታቸውን ዳዋ ያለብሰዋል፤
ድንኳኖቻቸውም እሾኽ ይወርሰዋል።
7የቅጣት ቀን መጥቶአል፤
የፍርድም ቀን ቀርቦአል፤
እስራኤልም ይህን ይወቅ!
ኀጢአታችሁ ብዙ፣
ጠላትነታችሁም ታላቅ ስለ ሆነ፣
ነቢዩ እንደ ሞኝ፣
*መንፈሳዊውም* ሰው እንደ እብድ
ተቈጥሮአል።
8ነቢዩ ከአምላኬ ጋር ሆኖ፣
የኤፍሬም ጠባቂ ነው፤[ሠ]
ዳሩ ግን በመንገዱ ሁሉ ወጥመድ፣
በአምላኩም ቤት ጠላትነት ይጠብቀዋል።
9በጊብዓ እንደ ነበረው፣
በርኵሰት ውስጥ ተዘፍቀዋል፤
እግዚአብሔር ክፋታቸውን ያስባል፤
ስለ ኀጢአታቸውም ይቀጣቸዋል።
10"እስራኤልን ማግኘቴ፣
የወይንን ፍሬ፣ በምድረ በዳ የማግኘት
ያህል ነበር፤
አባቶቻችሁንም ማየቴ፣
የመጀመሪያውን የበለስ ፍሬ የማየት
ያህል ነበር፤
ወደ ብዔልፌጎር በመጡ ጊዜ ግን፣
ለዚያ አሳፋሪ ጣዖት ራሳቸውን ለዩ፤
እንደ ወደዱትም ጣዖት የረከሱ ሆኑ።
11የኤፍሬም ክብር እንደ ወፍ በሮ
ይጠፋል፤
መውለድ፣ ማርገዝና መፀነስ የለም።
12ልጆችን ቢያሳድጉ እንኳ፣
ልጅ አልባ እስኪሆኑ ድረስ
እነጥቃቸዋለሁ፤
ፊቴን ከእነርሱ በመለስሁ ጊዜ፣
ወዮ ለእነርሱ!
13ኤፍሬምን እንደ ጢሮስ፣
በመልካም ስፍራ ተተክሎ አየሁት፤
አሁን ግን ኤፍሬም ልጆቹን፣
ለነፍሰ ገዳዮች አሳልፎ ይሰጣል።"
14*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስጣቸው፤
ምን ትሰጣቸዋለህ?
የሚጨነግፉ ማሕፀኖችን፣
የደረቁ ጡቶችን ስጣቸው።
15"በጌልገላ ካደረጉት ክፋታቸው ሁሉ
የተነሣ፣
እኔ በዚያ ጠላኋቸው፤
ስለ ሠሩት ኀጢአት፣
ከቤቴ አሳድዳቸዋለሁ፤
ከእንግዲህም አልወዳቸውም፤
መሪዎቻቸው ሁሉ ዐመፀኞች ናቸው።
16ኤፍሬም ተመታ፤
ሥራቸው ደረቀ፤
ፍሬም አያፈሩም፤

9፥4 ዘዳ26፥14፤ ኤር16፥7፤ ሕዝ4፥13-14፤ ሆሴ8፥13፤ ኢዩ1፥9፡13፤2፥14፤ ሐጌ 2፥13-14
9፥5 ኢሳ10፥3፤ ኤር 5፥31፤ ሆሴ2፥11
9፥6 ኢሳ5፥6፤19፥13፤ ኤር42፥22፤ ሆሴ 7፥11፤8፥13፤10፥8፤ ሶፎ1፥11
9፥7 1ሳሙ10፥11፤ ኢዩ31፥14፤ ኢሳ34፥8፤44፥25፤ ኤር10፥15፤16፥18፤29፥26፤ ሰቆ2፥14፤ ሕዝ14፥9-10፤ ሆሴ14፥1፤ ሚክ7፥14፤ ሉቃ21፥22
9፥8 ሕዝ22፥26፤ ሆሴ5፥1
9፥9 መሳ19፥16-30፤ ሆሴ4፥9፤5፥8፤8፥13፤ ሶፎ3፥7
9፥10 ዘኍ25፥15፤ መዝ106፥28-29፤ መሓ 2፥13፤ ኢሳ28፥15፤ ኤር11፥13፤ ሆሴ4፥14
9፥11 ቍ14፤ ኢሳ 17፥3፤ ሆሴ4፥7፤10፥5
9፥12 ቍ16፤ ዘዳ 31፥17፤ ሕዝ24፥21፤ ሆሴ7፥13
9፥13 ኢዮ15፥22፤ መዝ78፥67፤ ሰቆ2፥22፤ ሕዝ27፥3
9፥14 ቍ11፤ ሉቃ 23፥29
9፥15 ኢሳ1፥23፤ ኤር12፥8፤ ሆሴ4፥9፡15፤5፥2፤7፥2
9፥16 ቍ12፤ ኢዮ 15፥32፤ ሆሴ5፥11፤ 8፥7

[ሠ]8 *ወይም ነቢዩ የኤፍሬም ጠባቂ ነው፤ የአምላኬ ሕዝብ...*

ርኵስ መቈጠሩን ያመለክታል (አሞ 7፥17 እና *አግራጭ* ትርጕሙን ይመ)። የጣዖት አምልኮት ባስገኙት ልምላሜ የበቀለ በመሆኑ፣ በምድሩ የነበረውም ሰብል ሁሉ ርኵስ ነበር (ሕዝ 4፥13 ይመ)።

9፥4 *የሐዘንተኞች እንጀራ፤* በልቅሶ ቤት የሚቀርበው እንጀራ ርኵስ እንደ ሆነ ያመለክታል (ዘኍ 19፥14፤ ዘዳ 26፥14፤ ኤር 16፥7 ይመ)፤ የነካውም ሁሉ በሥርዐቱ መሠረት ርኵስ ይሆን ነበር። *ወደ እግዚአብሔርም ቤተ መቅደስ አይገባም፤* በምርኮ ጊዜ እስራኤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የምታቀርብበትና መንፈሳዊ በዓላቷን (ቍ 5) የምታከብርበት ቦታ አልነበራትም፤ ቀዳማዊ ኢዮርብዓም ያሠራቸውን ቦታዎች እንኳ (1ነገ 12፥28-33) ለዚህ ተግባር ልታውል አልቻለችም።

9፥6 *ግብፅ፤* 7፥16 እና ማብ ይመ። *ሜምፎስም፤* የታችኛው የሰሜን ግብፅ ዋና ከተማ ነው። *ዳዋ... እሾኽ፤* በኤዶም ላይ ከተነገረው ተመሳሳይ ፍርድ ጋር ያነጻጽሩ (ኢሳ 34፥13)።

9፥7 *መንፈሳዊውም ሰው፤* ሚክ 2፥11፤ 3፥8 ይመ። *እብድ፤* 2ነገ 9፥11፤ ኤር 29፥26 ይመ፤ ከኢሳ 21፥15 ጋር ያነጻጽሩ።

9፥8 *ጠባቂ፤* ኢሳ 56፥10፤ ኤር 6፥17፤ ሕዝ 3፥17፤ 33፥2-8 ይመ። *ወጥመድ... ጠላትነት፤* አስፈሪ ከሆነው ከባድ ጥፋት ሕዝቡን ያስጠነቅቁ ዘንድ እግዚአብሔር የላካቸውን ነቢያት እስራኤል በጠላትነት ተመለከተቻቸው (ኤር 1፥19፤ 11፥19፤ 15፥10፤ አሞ 7፥10-12) ይመ።

9፥9 *በጊብዓ እንደ ነበረው፤* በመሳ19-21 ላይ ስለ ተጠቀሰው ክፉ ድርጊት የሚናገር ነው። *በርኵሰት፤* የወርቅ ጥጃ ያመልኩ የነበሩትን እስራኤላውያንን ያመለክታል (ዘፀ 32፥7፤ ዘዳ 9፥12፤32፥5)። *እግዚአብሔር... ያስባል፤* በንስሓ ያልተስተካከለውና ከትውልድ ወደ ትውልድ በመምጣት የተከማቸው ኀጢአት (13፥12) ዘወትር ይታወሳል።

*9፥10፤* ቃል ኪዳናዊ ግንኙነት በመጀመሪያ የተደረገው በምድረ በዳ ነበር (2፥14-15፤ 13፥5፤ ዘዳ 32፥10 ይመ)። *የወይንን ፍሬ... የበለስ፤* ጥሩ ጣዕም ያላቸው ፍሬዎች ናቸው (ኢሳ 28፥4፤ ሚክ 7፥1 ይመ)። "የወይንን ፍሬ በምድረ በዳ፣ የመጀመሪያውን የበለስ ፍሬ" የሚለው ተምሳሌት፣ በሲና በተደረገው ቃል ኪዳን እስራኤል ከሌሎች ሕዝቦች ለይታ ራሷን ለእግዚአብሔር መስጠቷ፣ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘቱን በትክክል ይገልጻል። *ብዔልፌጎር፤* ቤትብዔልፌጎር በአጭሩ ሲጠራ ነው። ፌጎር ተራራ ነው (ዘዳ 3፥29)። ብዔልፌጎር ሲል የፌጎርን አምላክ የሚያመለክት (ዘኍ 25፥1-4) ሲሆን፣ ቤትፌጎር ማለትም "የፌጎር ቤተ መቅደስ" ከሚለው ጋር በተለዋጭነት ጥቅም ላይ ውሎአል (ዘዳ 3፥29፤ 4፥3፡46፤ ኢሱ 13፥20 ይመ)። እዚህ ላይ ሆሴዕ በዘኍ 25 ላይ የተጠቀሰውን ክስተት ያሳስባል። *የረከሱ ሆኑ፤* ኢሳ 5፥2፡4፡7 ይመ።

9፥11 *የኤፍሬም ክብር፤* የእስራኤልን የሕዝብ ብዛትና ብልጽግና የሚያመለክት ነው። የተሰጠው ቅጣት ለተሠራው ኀጢአት የሚገባ ነው። በግልሙትና የሕዝብ ቍጥር ሊጨምር አይችልም (4፥10 ይመ)።

9፥12 *ከእነርሱ፤* ለልጆቹ ማለት ነው።

9፥13 *ጢሮስ፤* በሀብቷ፣ ደስ በሚያሰኝ አካባቢዋና በአስተማማኝ ጸጥታዋ የታወቀች ነበረች (ሕዝ 27፥2-26 ይመ)።

*9፥14፤* ሆሴዕ የጸለየው በእስራኤል ላይ የበቀል ስሜት ኖሮት ሳይሆን፣ በኀጢአቷ ምክንያት የፈሰሰባትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቍጣ ተገቢ መሆኑን በመገንዘቡ ነው።

9፥15 *ጌልገላ፤* የ4፥15 ማብ ይመ። *ከቤቴ አሳድዳቸዋለሁ፤* አመንዝራይቱ ሚስት ከባሏ ቤት ተባራ እንደ ወጣች ሁሉ፣ እስራኤልም ከእግዚአብሔር ቤት ማለትም ከምድሩ ተባረረች (8፥1 እና ማብ ይመ)። *መሪዎቻቸው... ዐመፀኞች፤* በዕ

ልጆች ቢወልዱም እንኳ፣
ተንከባክበው ያሳደጓቸውን ልጆቻቸውን
እገድላለሁ።”

17 ባለመታዘዛቸው ምክንያት፣
አምላኬ ይጥላቸዋል፤
በአሕዛብም መካከል ተንከራታች
ይሆናሉ።

10 እስራኤል የተንዠረገገ ወይን
ነበር፤
ብዙ ፍሬም አፈራ፤
ፍሬው በበዛ መጠን፣
ብዙ መሠዊያዎችን ሠራ፤
ምድሩ በበለጸገ መጠን፣
የጣዖታት ማምለኪያ ዐምዶችን አስጌጠ።
2 ልባቸው አታላይ ነው፤
ስለዚህም በደላቸውን ይሸከማሉ።
እግዚአብሔር መሠዊያዎቻቸውን
ያወድማል፤
የጣዖት ማምለኪያ ዐምዶቻቸውን
ያፈራርሳል።

3 እነርሱም፣ “እኛ ንጉሥ የለንም፤
እግዚአብሔርን አላከበርንምና፤
ንጉሥ ቢኖረንስ፣
ምን ሊያደርግልን ይችል ነበር?” ይላሉ።
4 ከንቱ ተስፋ ይሰጣሉ፤
በሐሰት በመማል፣
ቃል ኪዳን ያደርጋሉ፤
ስለዚህም ፍርድ፣
በዕርሻ ውስጥ እንደሚገኝ መርዛማ ዐረም
ይበቅላል።
5 በሰማርያ የሚኖረው ሕዝብ፣
በቤት አዌን ስላለው የጥጃ ጣዖት ይፈራል፤
ሕዝቡም ያለቅስለታል፤
በክብሩ እጅግ ደስ ያላቸው ሁሉ፣
አመንዝራ ካህናትም እንደዚሁ
ያለቅሱለታል፤
በምርኮ ከእነርሱ ተወስዶአልና።
6 ለታላቁ ንጉሥ እንደ እጅ መንሻ፣
ወደ አሦር ይወሰዳል፤
ኤፍሬም ይዋረዳል፤
እስራኤልም ስለ ጣዖቱ ያፍራል።[o]
7 ሰማርያና ንጉሥዋ፣
በውሃ ላይ እንዳለ ኩበት ተንሳፍፈው
ይጠፋሉ።
8 የእስራኤል ኀጢአት የሆነው፣
የአዌን ማምለኪያ ኰረብታ ይጠፋል፤
እሾኽና አሜከላ ይበቅልባቸዋል፤
መሠዊያዎቻቸውንም ይወርሳል፤
በዚያን ጊዜ ተራሮችን፣ “ሸፍኑን!”
ኰረብታዎችንም፣ “ውደቁብን!” ይላሉ።

9 “እስራኤል ሆይ፤ ከጊብዓ ጊዜ ጀምሮ
ኀጢአት ሠራችሁ፤
በዚያም ጸናችሁ፤[ʺ]
በጊብዓ የነበሩትን ክፉ አድራጊዎች፣
ጦርነት አልጨረሳቸውምን?
10 በፈለግሁ ጊዜ እቀጣቸዋለሁ፤
ስለ ድርብ ኀጢአታችሁም ይቀጧቸው
ዘንድ፣
በእነርሱ ላይ ይሰበሰባሉ፤
11 ኤፍሬም ማበራየት እንደምትወድ፣
እንደ ተገራች ጊደር ነው፤
በተዋበ ጫንቃዋም ላይ፣
ቀንበርን አኖራለሁ፤
ኤፍሬምን እጠምዳለሁ፤
ይሁዳ ያርሳል፤
ያዕቆብም መሬቱን ያለሰልሳል።
12 ለራሳችሁ ጽድቅን ዝሩ፤
የጽኑ ፍቅርን ፍሬ ዕጨዱ፤
ዕዳሪውንም መሬት ዕረሱ፤
እርሱም መጥቶ፣
ጽድቅን በላያችሁ እስኪያዘንብ ድረስ፣
እግዚአብሔርን የምትፈልጉበት ጊዜ
ነውና።

13 እናንተ ግን ክፋትን ዘራችሁ፤
ኀጢአትንም ዐጨዳችሁ፤
የሐሰትንም ፍሬ በላችሁ።

9፥17 ዘዳ28፥65፤ ኤር6፥30፤ሆሴ4፥10፤ 7፥13
10፥1 1ነገ14፥23፤ሕዝ15፥2፤ሆሴ 3፥4፤4፥7፤8፥11፤ 12፥11፤13፥15
10፥2 ቈላ8፥1፤1ነገ 18፥21፤ሆሴ13፥16፤ ሚክ5፥13
10፥4 ሕዝ17፥19፤ ሆሴ4፥2፤አሞ5፥7፤ 6፥12
10፥5 ቈላ8፥ዘፀ32፥ 4፤መሳ18፥17፣18፤ 2ነገ23፥5፤ኢሳ44፥ 17፣20፤ሆሴ5፥8፤8፥5፤ 9፥1፣3፣11፤ሶፎ1፥4
10፥6 መሳ3፥15፤ 2ነገ16፥7፤ኢሳ30፥3፤ ኤር48፥13፤ሆሴ4፥7፤ 5፥13፤11፥5
10፥7 ቈላ15፤ ሆሴ13፥11
10፥8 ቈላ2፡5፤1ነገ 12፥28፣30፤ኢዮ30፥6፤ ኢሳ32፥15፤ሕዝ6፥6፤ ሆሴ4፥13፤9፥6፤አሞ3 ፥14፣15፤7፥9፤ሉቃ 23፥30፤ራእ6፥16
10፥9 ኢሱ7፥11፤ ሆሴ5፥8
10፥10 ሕዝ5፥13፤ ሆሴ4፥9
10፥11 ኤር15፥12፤ 13፥18
10፥12 ምሳ11፥18፤ መክ11፥1፤ኢሳ19፥ 22፤ 45፥8፤ኤር4፥3፤ ሆሴ12፥6፤ያዕ3፥18
10፥13 ኢዮ4፥8፤ መዝ33፥16፤ምሳ11፥ 18፤ሆሴ7፥3፤8፥7፤11 ፥12፤ገላ6፥7-8

[o]6 ወይም ስለ ምክሩ [ʺ]9 ወይም *በዚያም አቋም ወሰዳቸው*

ብራይስጥ ኀብረ አገላለጽ ነው።

9፥17 ***አምላኬ*** ከእንግዲህ ወዲህ እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ስላይደለ፣ ቃሉ የሆሴዕ ብቻ ነው። ***ይጥላቸዋል*** 4፥6፤ 2ነገ 17፥20 ይመ። ***ተንከራታች*** እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል የላከውን ማስጠንቀቂያ ባለመስማቷ፣ በዘዳ 28፥65-66 ላይ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ እስራኤል አገር አልባና የተበተነ ሕዝብ መሆን ነበረባት።

10፥1 ***እስራኤል*** በቅድመ አያቷ ስም በሰውኛ ዘይቤ የተጠራች አገር ናት። ***ወይን*** እስራኤልን የሚያመለክት ብዙ ጊዜ የሚጠቀስ ተለዋጭ ዘይቤ ነው (ዘዳ 32፥32፤ መዝ 80፥8-11፤ ኢሳ 5፥1፤ ኤር 2፥21 ይመ፤ ከዮሐ 15፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። ***በበለጸገ*** በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመን (793-753 ዓ.ቅ.ክ.) የነበረውን የብልጽግና ሁኔታ በማሰብ የተነገረ ሳይሆን አይቀርም።

10፥2 ***ልባቸው አታላይ ነው*** በመሠረቱ እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ (8፥2)፤ ነገር ግን ጣዖትን በማምለክ ክብሩን አቃለሉ።

10፥3 ***ንጉሥ የለንም*** አሦር አገሪቱን ባጠፋ ጊዜ ምን ዐይነት ሁኔታ ውስጥ እንደ ነበሩ ያመለክታል።

10፥4 ***ከንቱ ተስፋ ይሰጣሉ*** የመጨረሻዎቹ የእስራኤል ነገሥታት በጣም ብልሹዎችና አታላዮች ነበሩ።

10፥5 ***በሰማርያ*** የእስራኤል መናገሻ ከተማ ነበረች (የ7፥1 ማብ ይመ)። ***በቤት አዌን ስላለው የጥጃ ጣዖት*** ኢዮርብዓም በቤቴል ያሠራው ጣዖት ነው (1ነገ 12፥32-33 ይመ)።

10፥6 ***ኤፍሬም*** የሰሜኑን መንግሥት እስራኤልን ያመለክታል።

10፥8 ***ማምለኪያ ኰረብታ*** 4፥13-14 ይመ። ***ሸፍኑን… ውደቁብን!*** ተስፋ ከመቁረጥ የተነሣ የሚሰማ ጩኸት ነው፤ ኢየሱስም ይህንኑ ጠቅሶታል (ሉቃ 23፥30፤ እንዲሁም በራእ 6፥16 ተመልክቶአል፤ ኢሳ 2፥19 ይመ)።

10፥9 ***ከጊብዓ*** 9፥9 እና ማብ ይመ። በጊብዓ ላይ ጦርነት እንደ ሆነ ሁሉ፣ ጦርነትና ምርኮ በእስራኤል ላይ ይሆናል።

10፥11 ***እንደ ተገራች ጊደር*** እስከ አሁን ድረስ ኤፍሬም (እስራኤል) እህል በምትወቃበት ጊዜ በልታ እንደ ጠገበች ጊደር ሆናለች፤ አሁን ግን እግዚአብሔር እስራኤልና ይሁዳ ቀንበር ተጭኖባቸው አድካሚ የሆነ የዕርሻ ሥራ እንዲሠሩ ያደርጋል፤ ይህም በአሦራውያንና በባቢሎናውያን ተማርከው መሄዳቸውን የሚያመለክት ነው። ***ይሁዳ*** በመግቢያው ላይ ጸሓፊና የተጻፈ በት “ዘመን” የሚለውን ይመ።

10፥12 ***የጽኑ ፍቅርን ፍሬ ዕጨዱ*** እስራኤል ትክክለኛ የሆነውን ነገር ብቻ አድርጋ ቢሆን ኖሮ (“ጽኑ ፍቅር” የሚለው በዕብራይስጥ “ሒሴድ” ማለት ነው፤ የ6፥6 ማብ ይመ)፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን ትቀበል ነበር። ***ዕዳሪውንም መሬት ዕረሱ*** መሠረታዊ የሆነ አዲስ ጅማሬ በማድረግ ምርታማና ፍሬያማ በመሆን ንስሓ እንዲገቡና ከእንግዲህ ወዲህ ፍሬ አልባ እንዳይሆኑ ያሳስባል። ***ጽድቅን*** ለቃል ኪዳን አምላካቸው ፍጹም ታማኝ ሆነው ሲቆሙ፣ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በጽድቅ የሚያፈሰው በረከት ነው።

10፥13 ***የሐሰትንም*** እስራኤል አየማሽች ትኖር ነበር (7፥3፤ 10፥4፤

በራሳችሁ ጕልበት፣
በተዋጊዎቻችሁም ብዛት ታምናችኋልና፣
14 ስልማን፣ ቤትአርብኤልን በጦርነት ጊዜ
እንዳፈራረሰ፣
እናቶችንም ከልጆቻቸው ጋር በምድር
ላይ እንደ ፈጠፈጣቸው፣
ሽብር በሕዝብህ ላይ ይመጣል፤
ምሽጎችህም ሁሉ ይፈራርሳሉ፤
15 ስለዚህ ቤቴል ሆይ፤ ክፋትሽ ታላቅ ስለ
ሆነ፣
በአንቺም ላይ እንደዚሁ ይሆናል፤
ያ ቀን ሲደርስም፣
የእስራኤል ንጉሥ ፈጽሞ ይጠፋል።

## የእግዚአብሔር ፍቅር ለእስራኤል

11 “እስራኤል ገና ሕፃን ሳለ
ወደድሁት፤
ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት።
2 እስራኤል ግን አብዝቼ በጠራኋቸው[ሀ]
ቍጥር፣
አብዝተው ከእኔ[ለ] ራቁ፤
ለበኣል አማልክት ሠዉ፤
ለምስሎችም ዐጠኑ።
3 ኤፍሬምን እጁን ይዤ
እንዲራመድ ያስተማርሁት እኔ ነበርሁ፤
ነገር ግን የፈወስኋቸው እኔ እንደ ሆንሁ፣
እነርሱ አላስተዋሉም።
4 በሰው የርኅራኄ ገመድ፣
በፍቅርም ሰንሰለት ሳብኋቸው፤
ቀንበሩን ከጫንቃቸው ላይ አነሣሁላቸው፤
ዝቅ ብዬም መገብኋቸው።
5 “ታዲያ ንስሓ መግባትን እምቢ
በማለታቸው፣
ወደ ግብፅ አይመለሱምን?
አሦርስ አይገዛቸውምን?
6 በከተሞቻቸው ላይ ሰይፍ ይመዘዛል፤
የበሮቻቸውን መወርወሪያ ይቈርጣል፤
ስለ ክፉ ዕቅዳቸውም ይደመስሳቸዋል።
7 ሕዝቤ ከእኔ ዘወር ማለትን መረጡ፤
ወደ ልዑል ቢጣሩም፣
በምንም ዐይነት አያከብራቸውም።
8 “ኤፍሬም ሆይ፤ እንዴት እጥልሃለሁ?
እስራኤል ሆይ፤ እንዴትስ አሳልፌ
እሰጥሃለሁ?
እንዴት እንደ አዳማ አደርግሃለሁ?
እንዴትስ እንደ ሲባዮ እፈጽምብሃለሁ?
ልቤ በውስጤ ተናወጠ፤
ምሕረቴም ሁሉ ተነሣሥቶአል።
9 የቍጣዬን መቅሠፍት አላመጣም፤
ተመልሼም ኤፍሬምን አላጠፋም፤
እኔ በመካከላችሁ ያለሁ ቅዱስ ስምባክ ነኝ
እንጂ፣
ሰው አይደለሁምና፣
በቍጣ አልመጣም።[ሐ]
10 እግዚአብሔርን ይከተላሉ፤
እርሱም እንደ አንበሳ ያገሣል፤
እርሱ ሲያገሣ፣
ልጆቹ እየተንቀጠቀጡ ከምዕራብ
ይመጣሉ።
11 እንደ ወፍ ከግብፅ፣
እንደ ርግብ ከአሦር፣
እየበረሩ ይመጣሉ።
እኔም በቤታቸው አኖራቸዋለሁ፤”
ይላል እግዚአብሔር።

[ሀ]2 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራይስጡ ግን *በጠሯቸው* ይላል [ለ]2 ሰብዓ ሊቃናት እንዲሁ ሲሆን ዕብራይስጡ ግን *ከእነርሱ* ይላል [ሐ]9 ወይም *በማንኛውም ከተማ ላይ በተቃውሞ አልመጣም*

10፥14 2ነገ17፥3፤ ኢሳ13፥16፤17፥3፤ ሆሴ13፥16፤ሚክ5፥11
10፥15 ቍ7
11፥1 ዘፀ4፥22፤ዘዳ 4፥37፤ኤር2፥2፤ሕዝ 16፥22፤ሆሴ12፥9፡13 ፤13፥4፤ማቴ2፥5
11፥2 ቍ7፤2ነገ 17፥15፤ኢሳ65፥7፤ ኤር18፥15፤ሆሴ2፥13፤ 4፥13፤13፥1
11፥3 ዘፀ15፥26፤ ዘዳ1፥31፤32፥11፤ኤር 30፥17፤ሆሴ7፥15
11፥4 ዘፀ16፥32፤ ዘሌ26፥13፤መዝ78፥ 25፤ኤር31፥23፡20
11፥5 ዘፀ13፥17፤ ሆሴ7፥16፤10፥6
11፥6 ሰቆ2፥9፤ ሆሴ13፥16
11፥7 ቍ2፤ኢሳ26፥ 10፤ኤር3፥67፤8፥5
11፥8 ዘፍ14፥8፤ 1ነገ3፥26፤መዝ25፥6፤ ኤር7፥29፤ሰቆ3፥32፤ ሕዝ33፥11፤ ሆሴ6፥4፤አሞ7፥3
11፥9 ዘኍ23፥19፤ ዘዳ13፥17፤2ነገ19፥22 ፤ኢሳ31፥1፤ኤር18፥8፤ 30፥11፤ሰቆ3፥22፤ ሚል3፥6
11፥10 ዝ18፥45፤ ኢሳ31፥4፤42፥13፤ ሆሴ3፥5፤6፥13
11፥11 ዘፍ8፥8፤ኢሳ 11፥11፤ሕዝ28፥26፤ 34፥2528

12፥1 ይመ)።

10፥14 *ስልማን፣ ቤት አርብኤልን … እንዳፈራረሰ፤* ስሞቹ ይጠቀሱ እንጂ ታሪኩ በሚገባ የሚታወቅ አይደለም። በጥንት ጊዜ ጦርነት ሲካሄድ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ሕዝብን መጨፍጨፍ የተለመደ ነበር (ከ9፥13፤ 13፥16፤ 2ነገ 8፥12-13፤ መዝ 137፥8-9፤ኢሳ 13፥16፤ አሞ 1፥13፤ ናሆ 3፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

*11፥1፤* ለሦስተኛ ጊዜ ታሪክ መጠቀሱ (9፥10፤10፥9 ይመ)፣ እስራኤል በግብፅ ሳለች እግዚአብሔር እንደ መረጣት፣ ከዚያም አገር አውጥቶ መንግሥት ትሆን ዘንድ እንዳበቃት (ከ 12፥9፤ 13፥4 ጋር ያነጻጽሩ) ያመለክታል። እስራኤል ለእግዚአብሔር የሰጠችው ምላሽ የተገለጸው ለባሏ ታማኝ ባልሆነችው ሴት ተመስሎ ሳይሆን፣ በዐመፀኛ ልጅ ምሳሌ ነው (ከ1-3 ያሉትን ምዕራፎች ይመ)። የእስራኤልን ልጅነት በዘፀ 4፥22-23፤ ኢሳ 1፥2-4፣ የእግዚአብሔርን አባትነት ደግሞ በዘዳ 32፥6፤ በኤር 2፥14 ይመ። ለእስራኤል መመረጥ መሠረቱ (ከ3፥1 ጋር ያነጻጽሩ) የእግዚአብሔር ፍቅር እንደ ሆነ ሆሴዕ አስተውሎአል፤ ማቴዎስ፣ የእስራኤልን ከግብፅ መጠራት ለኢየሱስ ከግብፅ መመለስ በአምሳያነት ተጠቅሞበታል (ማቴ 2፥15 እና ማብ ይመ)።

11፥2 *ለምስሎችም፤* ዘዳ 7፥25፤12፥3 ይመ።

11፥3 *ኤፍሬምን፤* የሰሜኑን መንግሥት እስራኤልን ለማለት ነው። *እንዲራመድ፤* አባት ልጁ መራመድ እንዲችል የሚሰጠው ምሪት፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከታወቁት በጎ ተግባሮች አንዱ ነው። *የፈወስኋቸው፤* 5፥13፤ 6፥1፤ 7፥1 ይመ። *አላስተዋሉም፤* 2፥5-8 ይመ።

*11፥4፤* ምሳሌው ግልጽ አይደለም፤ ዘይቤያዊ አነጋገሩ ግን የሚያርስባቸውን በሬዎች በመጠበቅ ላይ ያለውን ገበሬ የሚያመለክት ይመስላል፤ ወይም አባት ወደ ጕንጩ አስጠግቶ የያዘውን ልጁን ያመለክታል። *መገብኋቸው፤* እግዚአብሔር እስደ ናቂ የሆነ ምግብ በበረሓ ሰጣቸው (ዘፀ 16፤ ዘዳ 8፥16 ይመ)።

11፥5 *ግብፅ… አሦር፤* 8፥13 እና ማብ እንዲሁም 9፥3 ይመ። ከቍ 1-4 የተጠቀሰው ርኅራኄ አዘል ቃል ተለውጦአል፤ ሁለቱ አገሮችም ስደት እንደሚጠብቃቸው ያመለክታል፤ እስራኤልም በእጃቿ ከሁለቱ በአንዱም አልጸናችም። እነዚህ ከግብፅ ነጻ ወጥተው የነበሩ ሕዝብ፣ ለታደጋቸው ለእግዚአብሔር ታማኞች ባለመሆናቸው ወደዚያው እንዲመለሱ መደረጉን የሚገልጽ ምጸታዊ አባባል ነው።

11፥7 *ወደ ልዑል ቢጣሩም፤* 7፥16 ይመ።

*11፥8፤* ዐመፀኛ ልጅ ዕድል ፈንታው በድንጋይ መወገር ነበር (ዘዳ 21፥18-21)፤ ነገር ግን የጌታ ርኅራኄ ከቍጣው በማየሉ፣ ኤፍሬምን ሊያጠፋው አልፈለገም። *አዳማ… ሲባዮ፤* ሰዶም በጠፋች ጊዜ (ዘፍ 19፥24-25፤ ዘዳ 29፥23፤ ኤር 49፥18) የፈረሱ ሜዳማ ከተሞች ሲሆኑ (ዘፍ 10፥19፤ 14፥2፡8)፣ ሙሉ በሙሉ መደምሰስን የሚያመለክቱ ናቸው።

11፥9 *በመካከላችሁ ያለሁ ቅዱስ፤* የኢሳ 1፥4፤ 6፥1 ማብ ይመ፤ ከኢሳ 12፥6 ጋር ያነጻጽሩ። የእግዚአብሔር ቅድስና በሆሴዕ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው። *አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና፤* እስራኤል ሰው እንደሚያደርገው ሁሉ ታማኝ ባትሆንም፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያሳየውን ፍቅር አያጥፍም (ቍ 1-4 እንዲሁም 1ሳሙ 15፥29፤ ሚል 3፥6 ይመ)። እስራኤል መቀጣቱን ተቀጥታለች፤ ሆኖም አልጠፋችም።

*11፥10፤* ከስደት መመለስን ያመለክታል። *እንደ አንበሳ ያገሣል፤* በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር እንደ አንበሳ ማግሣቱ ጥፋትን የሚያመለክት ማስፈራሪያ (ከ5፥14፤ 13፥7 ጋር ያነጻጽሩ) ሳይሆን፣ ከስደት መመለሳቸውን የሚያመለክት ነው። *ከምዕራብ፤* በባሕር ዳርቻ ያሉትን መሬቶችና ደሴቶችን ያመለክታል።

11፥11 *ከግብፅ… ከአሦር፤* 9፥3 ይመ። *እንደ ወፍ… እንደ*

## የእስራኤል ኀጢአት

12ኤፍሬም በሐሰት፣
የእስራኤልም ቤት በተንኰል ከበበኝ፤
ይሁዳ ለእምላክ የማይገዛ፣
የታመነውን ቅዱሱን የሚቃወም ነው።

**12** ኤፍሬም የነፋስ እረኛ ነው፤
ቀኑን ሙሉ የምሥራቅን ነፋስ
ይከተላል፤
ሐሰትንና ዐመፅን ያበዛል።
ከአሦር ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋል፤
የወይራ ዘይትንም ወደ ግብፅ ይልካል።
2እግዚአብሔር በይሁዳ ላይ የሚያቀርበው
ክስ አለው፤
ያዕቆብን[☒] እንደ መንገዱ ይቀጣዋል፤
እንደ ሥራውም ይከፍለዋል።
3በማሕፀን ሳለ የወንድሙን ተረከዝ ያዘ፤
ሙሉ ሰውም ሲሆን ከእምላክ ጋር ታገለ።
4ከመልአኩም ጋር ታገለ፤ አሸነፈውም፤
በፊቱ ሞገስን ለማግኘት አልቅሶ
ለመነው፣
እርሱንም በቤቴል አገኘው፤
በዚያም ከእርሱ ጋር ተነጋገረ፤
5እርሱም ሁሉን የሚገዛ አምላክ እግዚአብሔር፣
የሚታወቅበት ስሙም እግዚአብሔር
ነው።
6ስለዚህ ወደ አምላክህ ተመለስ፤
ፍቅርንና ፍትሕን ጠብቅ፤
ዘወትርም በአምላክህ ታመን።
7ነጋዴው በሐሰተኛ ሚዛን ይሸጣል፤
ማጭበርበርንም ይወዳል።
8ኤፍሬም እንዲህ እያለ ይታበያል፤
"እኔ ባለጠጋ ነኝ፤ ሀብታምም ሆኛለሁ፤
ይህ ሁሉ ሀብት እያለኝ፣
ምንም ዐይነት በደል ወይም ኀጢአት
አያገኙብኝም።"
9"ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ፣[ሀ]
አምላካችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤
በዓመት በዓላችሁ ቀን ታደርጉ
እንደ ነበረው ሁሉ፣
እንደ ገና በድንኳኖች እንድትቀመጡ
አደርጋችኋለሁ።
10ለነቢያት ተናገርሁ፤
ራእይንም አበዛሁላቸው፤
በእነርሱም በኩል በምሳሌ ተናገርሁ።
11ገለዓድ ክፉ ነው፤
ሕዝቡም ከንቱ ናቸው፤
ኮርማዎችን በጌልገላ ይሠዋሉን?
መሠዊያዎቻቸው በታረሰ መሬት ላይ
እንዳለ፣
የድንጋይ ክምር ይሆናሉ።
12ያዕቆብ ወደ ሶርያ[ሠ] ሸሸ፤
እስራኤል ሚስት ለማግኘት ሲል
አገለገለ፤
ዋጋዋንም ለመክፈል በጎችን ጠበቀ።
13እግዚአብሔር በነቢይ አማካይነት
እስራኤልን ከግብፅ አወጣ፤
በነቢይም በኩል ተንከባከበው።
14ኤፍሬም ግን ክፉኛ አስቈጣው፤

11፥12 ዘዳ7፥9፤ሆሴ 4፥2፤10፥13
12፥1 ዘፍ41፥6፤ 2ነገ17፥4፤መዝ78፥67 ፤ሕዝ17፥10፤ሆሴ4፥19፤5፥13፤7፥1፡11
12፥2 ዘፀ32፥34፤ ኢዮ10፥2፤ሆሴ4፥9፤ 9፥15፤አሞ2፥4፤ ሚክ6፥2
12፥3 ዘፍ25፥26፤ 32፥2429
12፥4 ዘፍ12፥8፤ 35፥15
12፥5 ዘፀ3፥15
12፥6 መዝ106፥3፤ ኢሳ19፥22፤ኤር4፥1፤ 22፥3፤ሕዝ18፥30፤ ሆሴ6፥13፤10፥12፤ ኢዩ2፥12፤ሚክ7፥7
12፥7 ዘሌ19፥36፤ አሞ8፥5
12፥8 መዝ62፥10፤ ሕዝ28፥5፤ራእ3፥17
12፥9 ዘሌ23፥43፤ ነህ8፥17፤ሆሴ2፥15፤ 11፥1
12፥10 መሳ14፥12፤ 2ነገ17፥13፤ሕዝ20፥49፤ኤር7፥25
12፥11 ሆሴ4፥15፤ 6፥8፤8፥11
12፥12 ዘፍ28፥5፤ 29፥18
12፥13 ዘፀ13፥3፤ 14፥1922፤ኢሳ63፥11 -14፤ሆሴ11፥1
12፥14 ሕዝ18፥13፤ ዳን11፥18

[☒]2 *ያዕቆብ ማለት ተረከዝ ይይዛል ማለት ሲሆን፣ ያታልላል ለማለት ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው*
[ሀ]9 *ወይም በግብፅ ከነበራችሁበት ጊዜ አንሥቶ*
[ሠ]12 *ሰሜን መስጴጦምያን ያመለክታል*

*ርግብ፤* ቀደም ሲል ከሰነፍ ርግብ (7፥11) ጋር በማነጻጸር እንደተ ገለጸው ሳይሆን፣ በፍጥነት መመለሳቸውን የሚያመለክት ነው (ከኢሳ 60፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። *ይላል እግዚአብሔር፤* 2፥13፡16፡21 ይመ።

11፥12 *በሐሰት ... በተንኰል፤* 7፥3፤ 10፥13 እና ማብ ይመ። *ይሁዳ፤* በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ፣ "ጸሐፊና የተጻፈ በት ጊዜ" የሚለውን ይመ። *ለአምላክ የማይገዛ፤* ኤር 2፥31 ይመ።

12፥1 *የነፋስ፤* 8፥7፤ መክ 1፥14 ይመ። *የምሥራቅን ነፋስ፤* 13፥15፤ ኢዮ 15፥2፤ 27፥21፤ ኢሳ 27፥8፤ ኤር 18፥17 ይመ። ነፋስ ይከተላል የሚለው ሐሳብ የእስራኤልን አንዴ ከግብፅ ጋር (2ነገ 17፥4፤ ኢሳ 30፥6-7) ሌላ ጊዜ ደግሞ ከአሦር ጋር (ከ5፥13፤ 7፥11፤ 8፥9፤ 2ነገ 17፥3 ጋር ያነጻጽሩ) ያደረገችውን ወላዋይ የውጭ ግንኙነት ያመለክታል።

12፥2 *በይሁዳ፤* በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ፣ "ጸሐፊና የተጻፈበት ጊዜ" የሚለውን ይመ። *ክስ፤* 4፥1 ይመ። *ያዕቆብን፤* እስራኤልን ያመለክታል (10፥11 ይመ)። እግዚአብሔር የያዕቆብ ትውልድ የሆኑትን ሁለቱን መንግሥታት ወቅሶአል፤ በሚያታል ሉበት ጊዜም ቢሆን፣ እስራኤልና ይሁዳ የቀደመውን የአባታቸ ውን ስም እንደሚያንጸባርቁ ያመለክታል።

12፥3 *በማሕፀን፤* ዘፍ 25፥26፤ 27፥36 ይመ። *የወንድሙን ተረከዝ ያዘ፤* የቍ 2 አግራጌ ትርጕም ይመ። የእግዚአብሔር የኪዳኑ ሕዝብ እንደ አባታቸው እንደ ያዕቆብ በማታለል ሕይ ወት ኖሩ፤ ያዕቆብ ወደ ቤቴል ለመመለስ እንደ ተጠራ ሁሉ፣ እነርሱም ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነበረባቸው (ዘፍ 35፥1-15)።

12፥4 *ከመልአኩም ጋር ታገለ፤* ዘፍ 32፥22-28 እና የዘፍ 32፥28 አግራጌ ትርጕም ይመ። *በቤቴል፤* ዘፍ 28፥12-19፤ 35፥1-15 ይመ። በሆሴዕ ዘመን፣ ቤቴል በሰሜኑ መንግሥት ውስጥ እጅግ የተከበረች የንጉሥ መናገሻ ነበረች (ከአሞ 7፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

12፥5 *ሁሉን የሚገዛ አምላክ እግዚአብሔር፤* በአሞ 3፥13፤ 6፥14፤ 9፥5 ላይ ከተጠቀሰው ጋር የሚጐዳኝ ነው።

12፥6 *ፍቅርንና፤* 6፥6 እና ማብ ይመ። *ፍትሕን፤* አሞ 5፥15፡24፤ ሚክ 6፥8 ይመ።

12፥8 *እኔ ባለጠጋ ነኝ፤* ሀብት በራሴ ብቁ ነኝ የማለትን ስሜት ያስከትላል (ከ10፥13፤ ከዘዳ 32፥15-18 ጋር ያነጻጽሩ)። *ምንም ዐይነት በደል... አያገኙብኝም፤* ኤፍሬም እንደ አታላይ ነጋዴ፣ የአታላይነት ተግባሯ (ከ11፥12 ጋር ያነጻጽሩ) እንደ ማይገለጥባት ርግጠኛ ነበረች።

12፥9 *አምላካችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤* 13፥4 ይመ፤ ከዘፀ 20፥2 ጋር ያነጻጽሩ። *በዓመት በዓላችሁ፤* የምድረ በዳውን ጕዞ ለማስታወስ ይደረግ የነበረው የዳስ በዓል (ዘሌ 23፥42-44) ሊሆን ይችላል። *በድንኳኖች፤* በድሮ ዘመን በምድረ በዳው ጕዞ ወቅት እንደ ነበረው ሁኔታ ማለት ነው (ከ2፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ)።

12፥10 *ለነቢያት ተናገርሁ፤* 6፥5፤ አሞ 2፥11፤ ዕብ 1፥1 ይመ። ብዙ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ነበር። *ራእይንም፤* መገ ለጥ ነው (ዘኍ 12፥6-8፤ አሞ 1፥1 ይመ)። *በምሳሌ፤* ከእግዚአብሔር የተሰጠ የማስጠንቀቂያ መልእክት የያዘ ነው (2ሳሙ 12፥1-4፤ መዝ 78፥2፤ ኢሳ 5፥17፤ ሕዝ 17፥2፤ 24፥3 ይመ)።

12፥11 *ገለዓድ ክፉ፤* 6፥8-9 እና ማብ ይመ። ከ734-732 ዓ.ቅ.ክ. አሦር ገለዓድን ወርራ ነበር (2ነገ 15፥29)። *በጌልገላ፤* 4፥15፤ 9፥15 ይመ። እንኳንስ አስተማማኝ ደኅንነት ሊሰጡ፣ የመሠዊያ ቦታዎቹ ራሳቸውም ይጠፋሉ። *በታረሰ መሬት ላይ፤* እስራ ኤላውያን ገበሬዎች በሚያርሱበት ጊዜ የፈነቃቀሉትን ድንጋ ዩች በአንድ ላይ ይከምሩአቸው ነበር።

*12፥12፤* ያዕቆብ ከዔሳው ሸሽቶ ወደ መስጴጦምያ ሄደ (ዘፍ 28፥2፡5)፤ በዚያም ሁለቱን የላባን ልጆች ለማግባት ሲል ስለ እያ ንዳንዳቸው ሰባት ሰባት ዓመት ተገዛ (ዘፍ 29፥20-28)፤ በኋላም የላባ እረኛ ሆኖ አገለገለው (ዘፍ 30፥31፤ 31፥41)።

12፥13 *በነቢይ፤* ሙሴን ማለቱ ነው (ከዘኍ 12፥6-8፤ ዘዳ 18፥15፤ 34፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። *ተንከባከበው፤* ያዕቆብ ለላባ በጎች እንደ ተጠነቀቀ ሁሉ፣ የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ በተንከራተተ ጊዜ እግዚአብሔር ተጠንቅቆለታል። የነቢዩ ሙሴ የቀድሞ አመራር እስራኤል አሁን ለነቢያት ካሳት ዝቅተኛ ግምት ጋር የሚነጻጸር ነው (ከ4፥5፤ 6፥5፤9፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

12፥14 *ኤፍሬም... አስቈጣው፤* እግዚአብሔር ቢያስጠንቅ

ጌታውም የደም አፍሳሽነቱን በደል በላዩ
ላይ ያደርግበታል፤
ስለ ንቀቱም የሚገባውን ይከፍለዋል።

## የእግዚአብሔር ቊጣ በእስራኤል ላይ

13 ኤፍሬም ሲናገር ሰዎች
ተንቀጠቀጡ፤
በእስራኤልም የተከበረ ነበር፤
ነገር ግን በኣልን ስላመለከ በደለ፤
ሞተም።
2 አሁንም ኀጢአትን መሥራት አበዙ፤
ብራቸውን አቅልጠው ለራሳቸው ባዕት
ሠሩ፣
በጥበብ የተሠሩ ምስሎችን አበጁ፤
ሁሉም የባለ እጅ ሥራ ናቸው።
ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ተብሎአል፤
"ሰውን መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ፤
የጥጃ ባዕቶችንም ይስማሉ"[ጨ]
3 ስለዚህ እንደ ማለዳ ጉም፣
ፈጥኖ እንደሚጠፋ የጧት ጤዛ፣
ከዐውድማ እንደሚጠረግ ዕብቅ፣
በመስኮትም እንደሚወጣ ጢስ ይሆናሉ።
4 "እኔ ግን ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ፣[ለ]
አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፤
ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም፤
ከእኔም በቀር ሌላ አዳኝ የለም።
5 በምድረ በዳ፣
በሐሩር ምድርም ተንከባከብሁህ።
6 ካበላኋቸው በኋላ ጠገቡ፤
በጠገቡ ጊዜ ታበዩ፤
ከዚያም ረሱኝ።

13፥1 መሳ8፥1፤ 12፥1፤ሆሴ11፥2
13፥2 1ነገ19፥18፤ ኢሳ44፥17፡20፤46፥6፤ ኤር10፥4፤44፥8፤ሆሴ 8፥4፤14፥3
13፥3 ኢዮ13፥25፤መዝ 1፥4፤68፥2፤ኢሳ17፥13፤ ዳን2፥35፤ሆሴ6፥4
13፥4 ዘፀ20፥3፤ዘዳ28፥ 29፤መዝ18፥46፤ኢሳ 43፥11፤45፥21-22፤ ኤር 2፥6፤ሆሴ2፥20፤12፥9
13፥5 ዘዳ1፥19
13፥6 ዘዳ32፥12፤ 15፡18፤ምሳ30፥7፡9፤ኢሳ 17፥10፤ኤር5፥7፤ሕዝ 28፥5፤ሆሴ2፥13፤4፥7
13፥7 ኢዮ10፥16፤ ኤር4፥7
13፥8 1ሳሙ17፥34፤ 2ሳሙ17፥8፤መዝ 17፥12፤50፥22፤ሰቆ 3፥10፤ሆሴ2፥12
13፥9 ዘዳ33፥29፤ ኤር2፥17፡19
13፥10 1ሳሙ8፥6፤ 2ነገ17፥4፤ሆሴ7፥7፤ 8፥4
13፥11 ዘኍ11፥20፤ ኢሱ24፥20፤1ሳሙ 13፥14፤1ነገ14፥10፤ ሆሴ3፥4፤10፥7
13፥12 ዘዳ32፥34
13፥13 2ነገ19፥3፤ ኢሳ13፥8፤66፥9፤ ሚክ4፥9፡10
13፥14 መዝ16፥ 10፤49፥15፤ኢሳ25፥ 8፤ሕዝ37፥12፡13፤ 1ቆሮ15፥55

7 ስለዚህ እንደ አንበሳ እመጣባቸዋለሁ፤
እንደ ነብርም በመንገድ አደባባቸዋለሁ።
8 ግልገሎቿን እንደ ተነጠቀች ድብ፣
እመታቸዋለሁ፤ እዘነጣጥላቸዋለሁ።
እንደ አንበሳም ስልቅጬ እውጣቸዋለሁ፤
የዱር አራዊትም ይገነጣጥላቸዋል።
9 "እስራኤል ሆይ፤ በእኔ ላይ ስለ ተነሣህ፣
ረዳትህንም ስለ ተቃወምህ ትጠፋለህ።
10 "ንጉሥንና አለቆችን ስጠኝ፤"
ብለህ እንደ ጠየቅኸው፣
ያድንህ ዘንድ ንጉሥህ የት አለ?
በከተሞችህ ሁሉ የነበሩ ገዦችህስ የት
አሉ?
11 በቍጣዬ ንጉሥን ሰጠሁህ፤
በመዓቴም ሻርሁት።
12 የኤፍሬም በደል ተከማችቶአል፤
ኀጢአቱም በመዝገብ ተይዞአል።
13 በምጥ ላይ እንዳለች ሴት ጭንቅ
ይመጣበታል፤
እርሱ ግን ጥበብ የሌለው ልጅ ነው፤
የሚወለድበት ጊዜ ሲደርስ፣
ከእናቱ ማሕፀን መውጣት
የማይፈልግ ሕፃን ነው።
14 "ከመቃብር ኀይል እታደጋቸዋለሁ፤
ከሞትም እቤዣቸዋለሁ፤
ሞት ሆይ፤ መቅሠፍትህ የት አለ?
መቃብር ሆይ፤[ሸ] ማጥፋትህ የት አለ?

[ጨ]2 ወይም *መሥዋዕት የሚያቀርቡ ሰዎች... ይስማሉ*
[ለ]4 ወይም *በግብፅ ከነበራችሁበት ጊዜ አንሥቶ*
[ሸ]14 በዕብራይስጥ ሲኦል ማለት ነው

---

ቀውም፣ ይህን ከማድረግ አልተመለሰም። *የደም አፍሳሽነቱ፤* ከ1፥4፤ 4፥2፤ 5፥2፤ 6፥8 ጋር ያነጻጽሩ። ይህ በነቢያት ላይ የተደረገውን ዐመፅ ወይም ሰውን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብን (ከ2ነገ 17፥17 ጋር ያነጻጽሩ) ሊያሳይ ይችላል። ከሕግ አንጻር (ዘሌ 20፥11-27) "ደማቸው በላያቸው ይሆናል" የሚለው ሐሳብ በደልን ያመለክታል። ነቢዩ፣ የቀድሞውን መለኮታዊ ጥበቃና ለቅጣት የሚዳርገውን የአሁኑን መለኮታዊ ቍጣ ያነጻጽራል። *የሚገባውን ይከፍለዋል፤* ኢሳ 65፥7 ይመ።

13፥1 *ኤፍሬም ሲናገር፤* ከያዕቆብ ባገኘው ቡራኬ (ዘፍ 48፥10-20)፣ ኤፍሬም የበረታ ነገድ ሆነ (መሳ 8፥1-3፤ 12፥1-7፤ 1ሳሙ 1፥1-4)፤ ከእርሱም እንደ ኢያሱና (ኢያ 24፥30) እንደ ናባጥ ልጅ እንደ ቀዳማዊ ኢዮርብዓም (1ነገ 11፥26፤ 12፥20) ያሉ ታዋቂ መሪዎች ወጡ። *በእስራኤልም፤* ዐሥሩ ሁሉቱን ነገዶች ያመለክታል። *ሞተም፤* የኀጢአት ደሞዝ ሞት ነው (ከሮሜ 6፥23 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የአገሪቱም ጥፋት በደጁ ነበረ።

13፥2 *ጣዖት፤* 4፥12፤ 8፥5-6፤ 11፥2 ይመ። *ሰውን መሥዋዕት፤* 2ነገ 17፥17፤ 23፥10፤ ሕዝ 20፥26፤ ሚክ 6፥7 ይመ፤ ከአማራጭ ትርጕሙ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ 1ነገ 12፥26-33 ይመ። *ይስሟቸዋል፤* ይህን የሚያደርጉት አክብሮትን ለመግለጽ ነው (ከ1ነገ19፥18 ጋር ያነጻጽሩ)።

*13፥3፤* "ጉም"፣ "ጤዛ" (6፥4 ይመ)፣ "ዕብቅ" (መዝ 1፥4፤ 35፥5፤ ኢሳ 17፥13፤ 29፥5 ይመ) እና "ጢስ" (መዝ 37፥20፤ 68፥2፤ ኢሳ 51፥6 ይመ) የተባሉት ኤፍሬም (እስራኤል) ፈጥኖ እንደምትጠፋ የሚያመለክቱ ዘይቤአዊ ቃላት ናቸው።

13፥4 *እኔ ... እግዚአብሔር ነኝ፤* 12፥9፤ ዘፀ 20፥2-3፤ ዘዳ 5፥6 ይመ። ይህም ኢዮርብዓም፣ አማልክቶችህ እነዚህ ናቸው ብሎ (1ነገ 12፥28) ከተናገረው ጋር የሚነጻጸር ነው። *አምላክ አታውቅም፤* 4፥1፤ 6፥3፤ 8፥2 ይመ።

13፥5 *በምድረ በዳ፤* 2፥14፤ 9፥10 ይመ።

13፥6 *ጠገቡ፤* ዘዳ 6፥11-12፤ 8፥10-14፤ 11፥15-16 ይመ። *ረሱኝ፤* ከዘዳ 8፥14፤ 31፥20፤ 32፥15፡18 ጋር ያነጻጽሩ።

*13፥7-8፤* ቀድሞ በምድረ በዳ የእስራኤል ጠባቂ የነበረው እግዚአብሔር (ቍ 5-6) አሁን አጥፊዋ ይሆናል፤ እንደ አንበሳ ይወጣታል፤ በድንገት በሰዎች ላይ ዘሎ ጉብ ለማለት እንዳደፈጠ ነብር ያደባባታል፤ ቅጣቱም የከፋ ይሆናል።

13፥7 *አንበሳ፤* 5፥14 ይመ። *ነብርም፤* ኤር 5፥6፤ ራእ 13፥2 ይመ።

13፥8 *ግልገሎቿን እንደ ተነጠቀች ድብ፤* 2ሳሙ 17፥8፤ 2ነገ 2፥24፤ ምሳ 17፥12 ይመ።

13፥9 *ረዳትህንም፤* መዝ 10፥14፤ 30፥10፤ 54፥4 ይመ።

13፥10 *ንጉሥህ የት አለ፤* ርዳታ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ ከነገሥታት ዘንድ አይገኝም። ነቢዩ በነበረበት ዘመን በነገሥታት ላይ የተፈጸመውን ግድያ ይጠቅሳል (3፥4፤ 7፥7፤ 8፥4፤ 10፥3 ይመ)። *ንጉሥ... ስጠኝ፤* በሳሙኤል ዘመን እስራኤል ሁሉ ንጉሥ እንዲያነግሥላቸው የጠየቁ ቢሆንም (1ሳሙ 8፥5፡20)፣ እዚህ ላይ የሚያመለክተው ስለ ሰሜኑ መንግሥት ብቻ ነው። ከዳዊት ቤት ከሆኑት ነገሥታት ይልቅ ቀዳማዊ ኢዮርብዓምን መረጡ (1ነገ 12፥26)።

*13፥11፤* ሕዝቡ ንጉሣዊ አገዛዝ መፈለጋቸው እንደ ዐመፅ ተቈጥሮአል (1ሳሙ 8፥7 ይመ)።

13፥12 *የኤፍሬም፤* የሰሜኑን መንግሥት እስራኤልን ያመለክታል። *በደል ተከማችቶአል፤* 9፥9 እና ማብ እንዲሁም ኢዮ 14፥17 ይመ። *ኀጢአቱም በመዝገብ፤* 7፥2፤ ዘዳ 32፥34-35 ይመ።

13፥13 *በምጥ ላይ እንዳለች...ጭንቅ፤* የነበሩበት ተስፋ የሚያስቈርጥ ሁኔታ፣ ምጥ ይዞአት ከምትጨነቅና (ኢሳ 13፥8፤ 21፥3፤ 26፥17፤ ኤር 4፥31፤ 13፥21፤ ሚክ 4፥9-10፤ ማቴ 24፥8 ይመ) ልጇም ሊወለድ ባለመቻሉ (2ነገ 19፥3፤ ኢሳ 37፥3 ይመ) ከምትሞት ሴት ጋር የሚነጻጸር ነው።

13፥14 *እቤዣቸዋለሁ፤* ከሞት ለማዳን የተሰጠ ተስፋ ነው። *ሞት፤* ቃሉ በሰዉኛ ዘይቤ የሕዝቡን ሞት ያመለክታል (ቍ 1 ይመ)። ጳውሎስ ይህን ክፍል ከትንሣኤ ጋር ያዛምደዋል (1ቆሮ 15፥55)። *መቃብር፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። በሲኦል ላይ የተሰጠውን ገለጻ ለመገንዘብ ኢዮ 3፥13-19፤ መዝ 18፥5፤ 116፥3፤ ኢሳ 14፥9-10 እንዲሁም የዘፍ 37፥35፤ የዮና 2፥2 ማብ ይመ።

"ከእንግዲህ ወዲህ አልራራለትም፤
15በወንድሞቹ መካከል ቢበለጽግም እንኳ፣
የምሥራቅ ነፋስ ከምድረ በዳ እየነፈሰ፣
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ ይመጣል፤
ምንጩ ይነጥፋል፤
የውሃ ጕድጓዱም ይደርቃል።
የከበረው ሀብቱ ሁሉ፣
ከግምጃ ቤቱ ይበዘበዛል።
16የሰማርያ ሰዎች በደላቸውን ይሸከማሉ፤
በአምላካቸው ላይ ዐምፀዋልና፤
በሰይፍ ይወድቃሉ፤
ሕፃናቶቻቸውም በምድር ላይ
ይፈጠፈጣሉ፤
የእርጉዝ ሴቶቻቸውም ሆድ ይቀደዳል።

## በረከትን ለማግኘት ንስሓ መግባት

**14** እስራኤል ሆይ፤ በኀጢአትህ
ምክንያት ስለ ወደቅህ፣
ወደ አምላክህ ወደ *እግዚአብሔር*
ተመለስ።
2የምትሉትን ቃል ይዛችሁ፣
ወደ *እግዚአብሔር* ተመለሱ፤
እንዲህም በሉት፤
"ኀጢአታችንን ሁሉ ይቅር በለን፤
የከንፈራችንንም ፍሬ እንድናቀርብ፣°
በምሕረትህ ተቀበለን።
3አሦር ሊያድነን አይችልም፤
በጦር ፈረሶችም ላይ አንቀመጥም፤
ከእንግዲህም የገዛ እጆቻችን የሠሯቸውን፣
'አምላኮቻችን' አንላቸውም፤
ድኻ አደጉ እንኳ ከአንተ ርኅራኄ
ያገኛልና።"

4"እኔ ከዳተኛነታቸውን እፈውሳለሁ፤
እንዲሁ እወዳቸዋለሁ፤
ቍጣዬ ከእነርሱ ተመልሶአልና።
5እኔ ለእስራኤል እንደ ጠል እሆናለሁ፤
እንደ ውብ አበባ ያብባል፤
እንደ ሊባኖስ ዝግባም፣
ሥር ይሰዳል፤
6ቅርንጫፉ ያድጋል፤
ውበቱ እንደ ወይራ ዛፍ፣
ሽታውም እንደ ሊባኖስ ዝግባ ይሆናል።
7ሰዎች እንደ ገና ከጥላው በታች ያርፋሉ፤
እርሱም እንደ እህል ይለመልማል፤
እንደ ወይን ተክል ያብባል፤
ዝናውም እንደ ሊባኖስ የወይን ጠጅ
ይወጣል።
8ኤፍሬም ሆይ፤ ከእንግዲህ ከጣዖት ጋር
ምን ጒዳይ አለኝ?^
የምሰማህና የምጠነቀቅልህ እኔ ነኝ፤
እኔ እንደ ለመለመ የጥድ ዛፍ ነኝ፤
ፍሬያማነትህም ከእኔ የተገኘ ነው።"
9ጥበበኛ የሆነ እነዚህን ነገሮች ያስተውላል፤
አስተዋይም እነዚህን ነገሮች ይረዳል።
*የእግዚአብሔር* መንገድ ቅን ነውና፤
ጻድቃን ይሄዱበታል፤
ዐመፀኞች ግን ይሰናከሉበታል።

*°2 ወይም እንደ ኮርማዎች መሥዋዕት የከንፈራችንን ፍሬ እንድናቀርብ*
*^8 ወይም ከእንግዲህ ከጣዖት ጋር ኤፍሬም ሌላ ምን አለው?*

13፥15 ኢዮ1፥19፤ ኤር20፥5፤51፥36፤ ሕዝ19፥12፤ሆሴ4፥19፤ 10፥1
13፥16 2ነገ8፥12፤ 15፥16፤17፥5፤ኢሳ 13፥16፤ሆሴ7፥14፤ 10፥2፡14፤11፥6፤አሞ 1፥13
14፥1 ኢሳ19፥22፤ ኤር3፥12፤ሆሴ4፥8፤ 5፥5፤9፥7
14፥2 ዘፀ34፥9፤መዝ 51፥16፡17፤ሚክ7፥18-19፤ዕብ13፥15
14፥3 ቍ8፤መዝ 10፥14፤33፥17፤68፥5፤ ኢሳ31፥1፤ኤር49፥ 11፤ሆሴ5፥13፤8፥6፤ 13፥2፤ሚክ5፥10.
14፥4 ኢዮ13፥16፤ ኢሳ30፥26፤55፥11 ኤር2፥19፤31፥20፤ ሆሴ6፥1፤ሶፎ3፥17
14፥5 ዘፍ27፥28፤ ኢዮ29፥19፤መሐ 2፥1፤ኢሳ18፥4፤35፥2
14፥6 መዝ52፥8፤ 92፥12፤መሐ4፥11፤ ኤር11፥16
14፥7 ዘፍ40፥10፤ መዝ91፥14፤ሕዝ 17፥23፤ሆሴ2፥22
14፥8 ቍ3፤ኢሳ 37፥24
14፥9 መዝ107፥ 43፤ 111፥7፥8፤ ምሳ10፥29፤ኢሳ1፥ 28፤26፥7፤ዳን12፥10፤ ሐሥ13፥10

13፥15 *ቢበለጽግም፤* በዕብራይስጥ ኤፍሬም ማለት ፍሬያማ ማለት ሲሆን፣ አንዱ እስራኤል አንዱ ደግሞ ኤፍሬም እያለ በማቀያየር የቀረበ ኀብረ አገላለጽ ነው። ድርቅን የሚያመጣው የምሥራቅ ነፋስ (ከኢዮ 1፥19፤ ከኢሳ 27፥8፤ ኤር 4፥11፤ 13፥24፤ 18፥17 ጋር ያነጻጽሩ) እዚህ ላይ የእግዚአብሔር መሣሪያ የሆነውን አሦርን ያመለክታል (ኢሳ 10፥5፡15)። በ734 ዓ.ቅ.ክ. አሦር የሰሜኑን መንግሥት ወረረ፤ ከዚያም ከ722-721 ዓ.ቅ.ክ. አገሪቱን ደምስሶ፣ ሕዝቡንም ማርኮ ወሰደ። *ሀብቱ ሁሉ፤* ናሆ 2፥9 ይመ።

13፥16 *የሰማርያ፤* 7፥1 እና ማብ እንዲሁም 8፥5-6፤ 10፥5፡7 ይመ። የሰሜኑ መንግሥት ለማለት ነው። *ዐምፀዋል፤* መዝ 5፥10፤ ሕዝ 20፥8፡13፡21 ይመ። *ሕፃኖቻቸው... ሴቶቻቸው፤* በሴቶችና በልጆች ላይ የተፈጸመውን ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ለመገንዘብ 10፥4፤ 2ነገ 8፥12፤ 15፥16፤ መዝ 137፥8-9፤ ኢሳ 13፥16፤ አሞ 1፥13፤ ናሆ 3፥10 ይመ።

14፥1 *ተመለስ፤* ንስሓ እንዲገባ የቀረበ ልዩ ጥሪ ነው (10፥12፤ 12፥6 ይመ)። በቍ 4-8 (ከመዝ 130፥7-8፤ ከኢሳ 55፥6-9 ጋር ያነጻጽሩ) ላይ በተሰጠው ተስፋ መሠረት ሕዝቡ የጸጋ ምላሽ ይቀበል ዘንድ ንስሓው እውነተኛ መሆን አለበት።

14፥2 *የምትሉትን ቃል ይዛችሁ፤* ማንም ሰው ባዶ እጁን አይቅረብ (ዘፀ 23፥15፤ 34፥20)፤ እውነተኛ የንስሓ ቃል እንጂ የእንስሳት መሥዋዕት ብቻውን በቂ አይደለም። *የከንፈራችንን ፍሬ፤* ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የምሥጋና መሥዋዕት ማለት ነው።

14፥3 *ድኻ አደጉ፤* የተጸጸተችውንና በሐዘን የተዋጠችውን እስራኤልን ያመለክታል (መዝ 10፥14፤ 68፥5፤ ሰቆ 5፥3 ይመ)። *ርኅራኄ ያገኛልና፤* ሎሩሃማ ከተባለችው ሕፃን ልጅ ስም ጋር ያነጻጽሩ (1፥6 እና ማብ እንዲሁም 2፥1፡23 ይመ)።

14፥4 *ከዳተኛነታቸውን፤* 11፥7 ይመ። *እፈውሳለሁ፤* 11፥3 ይመ። *እንዲሁ እወዳቸዋለሁ፤* ኢሳ 54፥6-8 ይመ። *እወዳቸዋለሁ፤* 3፥1፤ 11፥1፡8-9 ይመ። *ተመልሶአልና፤* ብዙ ጥፋት ካስከተለው የሚነድ ቍጣ ጋር ይነጻጸራል (8፥5 ይመ)።

14፥5 *ጠል፤* ጊዜያዊውን (ከ6፥4፤ 13፥3 ጋር ያነጻጽሩ) ሳይሆን፣ ዘላለማዊውን የእግዚአብሔርን በረከት (ከዘዳ 33፥13 ጋር ያነጻጽሩ) የሚያመለክት ነው። *ሊባኖስ ዝግባም፤* የመሳ 9፥15፤ 1ነገ 5፥6፤ ኢሳ 9፥10 ማብ ይመ። *ዝግባ፤* መዝ 80፥9-11 ይመ። *ሊባኖስ፤* መዝ 104፥16፤ ኢሳ 35፥2፤ 60፥13 ይመ።

14፥7 *ከጥላው፤* ከለላ ማለት ነው፤ ከመሳ 9፥15፤ ማሕ 2፥3፤ ሰቆ 4፥20፤ ሕዝ 3፥16 ጋር ያነጻጽሩ። *ወይን ተክል፤* 10፥1፤ ኢሳ 5፥1-7 ይመ።

14፥8 *ኤፍሬም፤* የሰሜኑን መንግሥት እስራኤልን ያመለክታል። *ዛፍ፤* በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በዚህ ክፍል ብቻ ነው በዛፍ የተመሰለው። የምሳሌውንም ሐሳብ በይበልጥ ለመረዳት ሕዝ 31፥3-7፤ ዳን 4፥12 ይመ። *ፍሬያማነትህ፤* ኤፍሬም ፍሬያማ የሆነው ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው (ከ2፥8 ጋር ያነጻጽሩ)።

14፥9 *የእግዚአብሔር መንገድ፤* መዝ 18፥21 ይመ፡ ሆሴዕ ለእያንዳንዱ አንባቢ የመራመድ ወይም የመሰናከል ማለትም የመታዘዝ ወይም የዐመፅ ምርጫ በማቅረብ (ከ4፥5፤ 5፥5 ጋር ያነጻጽሩ) መልእክቱን ይደመድማል።